# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 352 ነሐሴ 22 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# “ስለ ዓይን ባንክ የተሻለ ግንዛቤ መፍጠር ይገባል”

## የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ

### ከ14 ሺህ በላይ ዜጎች የዓይን ብሌናቸውን ለመለገስ ቃል ገብተዋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- ስለኢትዮጵያ የዓይን ባንክ በማኅበረሰቡ ዘንድ ከዚህ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው መሥራት እንደሚገባ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ አሳሰቡ።

የኢትዮጵያ የዓይን ባንክ የተመሰረተበት 20ኛ ዓመት “ብርሃን ይስጡ፤ ብርሃን አይቅበሩ” በሚል መሪ ቃል ተከብሯል።

በክብረ በዓሉ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ዓይን ባንክ ብርሃን ላጡ ዜጎች ብርሃናቸው እንዲመለስ እያደረገ ያለው ተግባር የሚመሰገን ነው። ስለ ዓይን ባንኩም በማኅበረሰቡ ዘንድ ከዚህ የተሻለ የግንዛቤ ሥራ መሥራት ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ብርሃን ማጣት እንደማይመለስ ብዙ ዜጎች ቢያስቡም፤ ይህንን ችግር መቅረፍ እንደሚቻል የኢትዮጵያ የዓይን ባንክ አሳይቶናል፤ ተቋሙ አሁን ያለበት ደረጃም ተስፋ ሰጪ ነው ብለዋል።

በአብዛኛው ዜጋ ዘንድ ስለዓይን ብሌን ልገሳ ግንዛቤው ባለመኖሩ የዕድር ማኅበራትና ሌሎች ተቋማትን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊሠራ እንደሚገባ አመላክተዋል። አሁን ላይ እየተሠራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ድጋፋቸውን ለመስጠት ዝግጁ እንደሆኑ ፕሬዚዳንቷ ጠቁመዋል።

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ በበኩላቸው፤ ተቋሙ ላለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል፤ የበርካታ ዜጎችን የማየት ተስፋን በመለወጥ እይታን እየሰጠ ይገኛል ነው ያሉት።

የዓይን ብሌን ጥራት ባለው መልክ በመሰብሰብ ተገቢውን አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ ያነሱት ዶክተር ሊያ፤ ተቋሙ ሥራውን ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲሠራ የራሱ በጀትና አደረጃጀት እንዲኖረው መደረጉ ለስኬቱ የሚያግዘው ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ የደምና ኅብረህዋስ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ዜጎች የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ እንደሚያስፈልጋቸው በቅርቡ የተሠራ ጥናት ያመለክታል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ የደምና ኅብረህዋስ ባንክ አገልግሎት ስር የኢትዮጵያ የዓይን ባንክ ዘርፍ

ስለዓይን ባንክ የተሻለ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን ለማድረግ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍን ማጎልበት ያስፈልጋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን ለማድረግ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ማጎልበት የሚያስፈልግ መሆኑን የኢፌዴሪ ሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል ገለጹ፡፡

የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት በ2014/2015 ዓ.ም በተለያዩ የሙያ ዘርፎች በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ያሰለጠናቸውን ሦስት ሺህ 651 ሠልጣኞች ትናንት አስመርቋል፡፡

የኢፌዴሪ ሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል በዕለቱ እንደተናገሩት፤ የሚመረቁ ሠልጣኞች ከሥራና ሥራ ስምሪት ጋር በማስተሳሰርና ኢንዱስትሪው የሚፈልገው ብቁ ዜጋ ለማፍራት የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሚና ወሳኝ ነው።

እንደሀገር ለማሳካት የታቀደውን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን ለማድረግ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ማጎልበት እንደሚያስፈልግ የጠቆሙት ሚኒስትሯ፤ ቴክኒክና ሙያ እውቀት፣ ክህሎትና ጥበብ የሚገኝበት ዘርፍ በመሆኑ ገበያው የሚፈልገውን ሙያ ለማፍራት እንደሚረዳ ተናግረዋል፡፡

ሚኒስትሯ አክለውም፤ ኢንስቲትዩቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በመደበኛ መልኩ የ12ኛ ክፍል ፈተና ላይ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበው ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩ 521 ተማሪዎች ማስመረቁ በዘርፉ ላይ የነበሩ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የቀየረ በመሆኑ የዘንድሮው ምርቃት ልዩ ያደርገዋል ብለዋል፡፡

የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA
የዜጎች ጤና ለሃገር ብልጽግና!
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!

# የጤና ኤክስቴሽን መርሀ ግብር በሽታን ቀድሞ ለመከላከል አወንታዊ ሚና ተጫውቷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የእናቶችና ሕፃናት ሞትን መቀነስና ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ቀድሞ መከላከል መቻሉን የጤና

የጤና ኤክስቴሽን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ተቋርጦ የነበረው የሕዳሴ ግድብ የሦስትዮሽ ድርድር በካይሮ ተጀመረ

ገጽ 6





















## “ግብረሰዶም በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የማይደገፍ ፅዩፍ ተግባር ነው”

*- መጋቤ ቸርነት በላይ*

**ዳግማዊት ግርማ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የግብረሰዶም ወንጀል በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የማይደገፍ ፅዩፍ ተግባር መሆኑን መጋቤ ቸርነት በላይ ተናገሩ፡፡ ወንጀሉ የሰው ዘርን የማጥፋት ሃሳብ መሆኑን አውቆ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያወግዘው እንደሚገባም አመላከተዋል፡፡

መጋቤ ቸርነት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የግብረሰዶም ወንጀል ከኢትዮጵያዊ ማንነት ያፈነገጠ ነውር ተግባር ሲሆን፤ በሀገሪቷ በየትኛውም ባህል ተቀባይነት የሌለው ፅዩፍ ተግባር ነው።

እንደ መጋቤ ቸርነት ንግግር፤ ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የመከባበር፣ የመዋለድ ባህልና የመስፋት ታሪክ አላት፤ የጋብቻ ሥርዓቷንም በሚመለከት በባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ሕጋዊ መንገድ የሚፈጸም የጋብቻ ሥርዓት ያላት ሀገር ናት፡፡ ወንጀሉ ይህን የሚፃረር ነው፡፡

የግብረ ሰዶም ወንጀል የጋብቻ ጠላት የሆነ እርኩስ መንፈስ ሥራ ነው ያሉት መጋቤ ቸርነት፤ ዘርን የሚያስቀጥሉ ብዙ ተባዙ የሚለውን አምላካዊ ሃሳብ እንዳይቀጥል የሚያደርግ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

“ወንጀሉ በሕገ እግዚአብሔር ነውር፤ በክርስትና እምነትም ላይ የተወገዘ ነው” ያሉት መጋቤ ቸርነት፤ ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ እግዚአብሔር የሚያስቆጣው ነገር ያስቆጣዋልና የግብረ ሰዶም ወንጀልን ማውገዝ ይገባዋል ብለዋል፡፡

በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የግብረሰዶም ወንጀል የሚሳተፉ ጥፋተኞች የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው፤ ከተማን ያስጠፉ ከባድ ነውር የሆነ ወንጀል ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እንደ መጋቤ ቸርነት ገለጻ፤ የግብረሰዶም ወንጀልን በሚመለከት ቆራጥ የራስ የሆነ አቋም ምልከታና ሃሳብ ያስፈልጋል፤ እድገት ሥልጣኔ ዘመናዊነት ነው እያሉ ከምዕራቡ ዓለም የመጣን ነገር ሁሉ ማስተናገድ የመውደቅ ምልክት ነው፡፡

አንዳንድ ነገሮችን በማቃለልና ዘመናዊነት ነው ብሎ በማሰብ ከቸልተኝነት ከሚመጡ ጥፋቶች በመታቀብ መኖር እንደሚገባ ያመላከቱት መጋቤ ቸርነት፤ ኅብረተሰቡን ስለወንጀሉ አስከፊነት በማሳወቅና በማስተማር ኅብረተሰቡ መሰል ወንጀሎችን መከላከል ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ አኩሪ የሆነ ባህላዊ ማንነት እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅኝትና መልክ ያላት ሀገር በመሆኗ ይህንን በሚመጥን መልኩ ልጆቻችንን በማስተማር የግብረሰዶም ወንጀል ፈፃሚዎችንም መቃወም ያስፈልጋል ሲሉም መጋቤ ቸርነት አሳስበዋል፡፡

ወንጀሉ በልጆች፣ በትውልድና በሰው ዘር ላይ የሚመጣ ጨካኝ እሳቤ ውጤት እንዲሁም እምነት የለኝም የሚል ሰውን ሳይቀር የሚመለከት ነው ያሉት መጋቤ ቸርነት፤ ችግር ሲመጣ ብቻ ሳይሆን የወንጀሉን ፈፃሚዎች ሁልጊዜ መቃወም እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

መንግሥት የግብረሰዶም ወንጀል ፈፃሚዎች ላይ የጸና አቋም መያዝ አለበት፤ በማኅበረሰብ የተወገዘውን ትልቅ ነውር እንዳይፈፀም አስተማሪ እርምጃዎች መወሰድ ይገባቸዋል፡፡ ግለሰቦች፣ የፀጥታና የእምነት ተቋማትም በዚህ ጉዳይ ላይ በጋራ በመቆም ሊያወግዙ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

የወንጀሉ ፈፃሚዎች ያለ የሌለ አቅማቸውን ተጠቅመው ጉዳዩ ላይ በመሥራት ላይ ናቸው ያሉት መጋቤ ቸርነት፤ ወንጀሉ የሰው ዘርን የማጥፋት ሃሳብ መሆኑን አውቆ የሚዲያ ባለሙያዎችን ጨምሮ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያወግዘው ይገባልም ነው ያሉት፡፡

# በከተማዋ ወንጀልን ለመከላከል የንግድ ተቋማት የደህንነት ካሜራ እንዲገጥሙ የሚያስገድድ መመሪያ ወጣ

**አማን ረሺድ**



<u>አዲስ አበባ፡-</u> በሀዋሳ ከተማ ተደጋጋሚ የስርቆት ወንጀሎችን ለመከላከል የንግድ ተቋማት የደህንነት ካሜራ እንዲገጥሙ የሚያስገድድ መመሪያ ማውጣቱን የሲዳማ ክልል ሰላምና ፀጥታ ቢሮ አስታወቀ፡፡ መመሪያው በአነስተኛ የንግድ ተቋማት ላይ ተግባራዊ እንደማይሆን ተገልጿል።

የቢሮው ኃላፊ አቶ አለማየሁ ጢሞቲዮስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀዋሳ ከተማ በሚገኙ አንዳንድ ድርጅቶች አካባቢ በተደጋጋሚ የተሽከርካሪና የሞተር ሳይክል ስርቆቶች ተፈጽመዋል። በዚህ የተነሳ ወንጀሉን ለመቆጣጠር የንግድ ተቋማት የደህንነት ካሜራ እንዲገጥሙ የሚያዝ መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ብለዋል።

እንደ አቶ አለማየሁ ገለጻ፤ የደህንነት ካሜራው በሆቴሎች፣ በምሽት ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በሆስፒታሎች፣ በባንኮችና ዓለም አቀፍ ሆቴሎች ላይ ተግባራዊ ይሆናል። በመመሪያው መሠረት በከተማዋ የሚገኙ የንግድ ተቋማት በድርጅታቸው ውስጥና ወደ ውጪ የሚመለከቱ የደህንነት ካሜራዎችን መግጠም እንደሚገባቸው አቶ አለማየሁ ገልጸዋል።

የደህንነት ካሜራዎቹ በግዢ ደረጃ ዋጋቸው ከፍተኛ በመሆኑ መመሪያው አነስተኛ የንግድ ተቋማት ላይ ተግባራዊ እንደማይደረግ አቶ አለማየሁ ገልጸዋል። የክልሉ መንግሥት አነስተኛ የንግድ ተቋማት በብዛት በሚገኙባቸው አካባቢዎች የፖሊስ ማዕከላትን እየገነባ መሆኑን ጠቁመዋል።

መመሪያው የሚይዛቸው የንግድ ተቋማቶች የሚገጥሟቸው የደህንነት ካሜራዎች በአራቱም አቅጣጫ እስከ 500 ሜትር ርቀት ላይ ያሉ ጉዳዮችን ጭምር መቆጣጠር የሚያችሉ መሆን እንዳለባቸው አቶ አለማየሁ አስረድተዋል።

የደህንነት ካሜራዎቹ መገጠም የጸጥታ ኃይሉ በሌለበት ጊዜ የሚፈጸሙ ወንጀሎችንና ስውር ስርቆቶችን ለመቆጣጠር እንደሚረዳ አቶ አለማየሁ ተናግረዋል።

ለደህንነት ካሜራ ገጠማው በቂ የሰው ኃይል ሥልጠና በከተማ ደረጃ እየተሰጠ መሆኑን አመላከተዋል። የንግድ ተቋማቱ አዲሱን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የአንድ ወር የጊዜ ገደብ እንደተሰጣቸው አስታውቀዋል፡፡

መመሪያውን ተግባራዊ የማያደርጉ ተቋማትን በተመለከተ ዝርዝር የቅጣት ደረጃ በቀጣይ ጊዜያት ይወጣል ብለዋል። ኅብረተሰቡም መንግሥት የሕዝቡን ደህንነት ለማስጠበቅ በሚሠራው ሥራ ተባባሪ ሊሆን እንደሚገባ አቶ አለማየሁ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡



# የእግር ኳስ ዘርፉን በዘላቂነት የሚያግዝ የስፖርት ትጥቅ ድጋፍ ስምምነት ተደረገ

**ዳግማዊት አበበ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን የስፖርት ትጥቅ እጥረትን ለመፍታት የሚያስችል ስምምነት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ከጎፈሬ ሀገር በቀል የትጥቅ አምራች ድርጅት ጋር ተፈራረመ። ስምምነቱ የእግር ኳስ ስፖርት ዘርፉን በዘላቂነት ለማሳደግ የሚያስችል እንደሆነም ተጠቁሟል፡፡

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራ በስምምነት መርሀ ግብሩ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ የስፖርት ትጥቅ እጥረትን ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትኩረት እየተሰራበት ይገኛል፡፡ በተፈረመው ስምምነትም ፕሮጀክቱ ያለበትን መሠረታዊ የትጥቅ ችግር ለመፍታት ትልቅ እገዛ የሚያደርግ ሲሆን የእግር ኳስን በዘላቂነት ለማሳደግም የሚያግዝ ነው፡፡

አሁን ላይ ለ970 ተጫዋቾች እና ለ135 አሠልጣኞች የትጥቅ ድጋፍ ተደርጎላቸው የምዘና ውድድር እያደረጉ ይገኛሉ ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ስምምነቱም ቀጣይነት ያለው ሥራ ለመሥራት እንደሚያስችላቸው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ደረጀ ቱፋ እንዲሁም የጎፈሬ የስፖርት ትጥቅ አምራች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ አቶ ሳሙኤል መኮንን በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቱ የነገውን የሀገሪቱን ተተኪ እግር ኳስ ተጫዋቾች ለማፍራት አይነተኛ አስተዋጽኦ ስላለው ድጋፉና ስምምነቱ እንደ ውጤታማነት የሚታይ ነው፡፡ በዚህም ለፕሮጀክቱ ስኬታማነት አብሮ ለመሥራት ዝግጁ ነን ብለዋል፡፡

የስፖርት ትጥቅ ወጪውን 70 በመቶ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲሁም ጎፈሬ ትጥቅ አምራች ድርጅት 30 በመቶ ወጪውን እንደሚሸፍን በስምምነቱ ወቅት ተጠቅሷል፡፡



## "ዓለም የምትገነባው በበጎ ፈቃደኞች መልካም ሥራ በመሆኑ ተግባሩ ዓመቱን ሙሉ ሊሠራበት ይገባል"

- መምህር አካሉ አብርሃም

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም የምትገነባውም፤ የተገነባችውም በበጎ ፈቃደኞች መልካም ሥራ በመሆኑ በጎ ፈቃደኝነት ዓመቱን ሙሉ ሊሠራበት ይገባል ሲሉ ፓን አፍሪካኒስት መምህር አካሉ አብርሃም ተናገሩ፡፡

መምህር አካሉ አብርሃም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በዓለም ላይ የሚኖረው ሕዝብ ሁሉም የራሱ መተዳደሪያ ሥራ ኖሮት ሳይሆን የሚኖረው አንዱ ሌላውን በመደገፍና በጎ ሥራ በመሥራት ነው፡፡ ዓለም የምትገነባውም፤ የተገነባችውም በበጎ ፈቃደኞች መልካም ሥራ በመሆኑ በጎ ፈቃደኝነት ዓመቱን ሙሉ ሊሠራበት ይገባል።

ስለሆነም ይህ ትልቅ ሥራ የጊዜ ገደብ ሳይደረግለትና የክረምት ብቻ ንቅናቄ ተደርጎ ሳይታሰብ ዓመቱን ሙሉ ሊሠራበት የሚገባ እና እንደ ጥሩ ባህል ሊለመድ የሚገባው ነው ብለዋል፡፡

እንደ መምህሩ ገለጻ በአሁኑ ወቅት ዓለምን የሚያንቀሳቅሱ ትልልቅ ተቋማት ጭምር በውስጣቸው የበጎ ፈቃድ ተቋማትና ግለሰቦች እንዳላቸው በመጥቀስ፤ እነዚህ ተቋማት ኢትዮጵያን ጨምሮ በተለያዩ ሀገራት በመልካም ሥራ እየተንቀሳቀሱ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያም የራሷን እሴት በማከል የበጎ ፈቃድ ሥራዎችን ከዚህ በበለጠ ልትሠራ ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የበጎ ፈቃድ ተቋማት እንደ መቄዶንያ፣ ኦቲዝም ሴንተር፣ አበበች ጎበና እና ሌሎች እንደ አብነት የሚጠቀሱ ቢሆኑም፤ ሁሉም ዜጋ ልክ እንደ ተቋማቱ ግድ ሰጥቶት ሊሠራ እንደሚገባውም ገልጸዋል፡፡

በጎ ፈቃደኝነት በተለይ ለተማሪዎች የክረምት ሥራ ብቻ ተደርጎ መታሰብ እንደሌለበትና፤ አስተማሪዎችም በመማር ማስተማር ሂደት ላይ እንደ የቤት ሥራ እየሰጡ ልምድ ሊያደርጉ እንደሚገባ የገለፁት መምህሩ፤ እሳቸው ይህን ተግባር በተማሪዎቻቸው ላይ ይተገብሩት እንደነበርና ጥሩ ልምድ እንዳገኙበትም ጠቅሰዋል፡፡

ትምህርት ቤቶችም ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመሆን እንደ ክበቦችንና ሌሎች ሙሉውን ዓመት በፕሮግራም በመጠቀም ቅዳሜ እና እሁድንም በማካተት በጎ ፈቃደኝነት እንዲለመድ ትኩረት አድርገው ሊሠሩ ይገባል ብለዋል፡፡

የበጎ ፈቃድ ሥራ ከንቅናቄ በዘለለ የአዘቦት ተግባር ቢሆን ሀገርን ወደ ተሻለ ዕድገት ለማሻገርና ዜጎችም በመልካም ሥነ ምግባር እንዲታነፁ፤ ሰላም እና አንድነት የሰፈነባት ሀገር እንድትኖረን የሚረዳ ነው ሲሉም አብራርተዋል፡፡

ሀገራችን ላይ በበጎ ፈቃድ የታነፀ ትውልድ በተበራከተ ቁጥር በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በአካባቢ ጥበቃ ሁሉንም ለማሳደግ የሚጠቅም ሲሆን፤ ትንሽ ወጪ ተጠቅመን በቢሊዮን የሚቆጠር ወጪ በሰው ኃይል መሸፈን እንደሚቻልና በተለይ ትውልድ በመልካም ሥነ ምግባር ለማነፅ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው ብለዋል፡፡

በጎ ፈቃደኝነት ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት የተናገሩት መምህሩ፤ ራስን ለማስተካከልና ጤናማ አስተሳሰብ ለመገንባት፣ አእምሮ እንዲታደስም ትልቅ ሚና አለው፡፡ ስለሆነም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በቅድመ አንደኛ ደረጃ እና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትኩረት ተደርጎ ሊሠራበት እንደሚገባ በመጥቀስ፤ ሁሉም ሃይማኖቶች ሌላውን በማይነካ መንገድ ከሠሩበት ነገ የተሻለች ሀገር እንገነባለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

# የውሃ ዲፕሎማሲን በምርምር የሚደግፍ ወጥ ተቋም ለመገንባት እየተሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**



ዶክተር ቦጋለ ገብረማርያም



ዶክተር ለሚ ጉታ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን የውሃ ሀብት እና ዲፕሎማሲ በምርምር የሚደግፍ ወጥ ተቋም ለመገንባት እየሠሩ መሆኑን ዩኒቨርሲቲዎች ገለጹ።

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ለሚ ጉታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ሀብትን በሳይንሳዊ መንገድ ለማጥናት እና የኢትዮጵያን ጥያቄዎች ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማሳወቅ ከፍተኛ ሥራዎችን ለመሥራት እቅድ ይዟል።

ዩኒቨርሲቲው ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በዚህም ዩኒቨርሲቲው የኢትዮጵያን የውሃ ሀብት እና ዲፕሎማሲ በምርምር የሚደግፍ ወጥ ተቋም ለመገንባት ከሚሠሩ ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ እየሠራ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን በአግባቡ እየተጠቀመችበት አለመሆኑ ከዓባይ ግድብ ጋር በተያያዘ ጎልቶ ወጥቷል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በተለይ ኢትዮጵያ ከዓባይ ወንዝ መጠቀም የሚገባትን እንድታገኝ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተለያዩ ጥረቶች ሲያደርጉ ቆይተዋል ብለዋል።

ነገር ግን አሠራሩ በተናጥል ከመሆኑ አንፃር ተጽዕኖ ፈጣሪ ውጤቶችን ሊያስገኝ አልቻለም። በአሁኑ ሰዓት የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ አራት የከፍተኛ ተቋማት ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የውሃ ሀብት ዲፕሎማሲ ፎረም ላይ እየተሳተፉ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በዚህ ፎረም በውጭ ሀገራት ያሉ ተጽዕኖ ፈጣሪ ኢትዮጵያውያን ይሳተፋሉ። የኢትዮጵያ የውሃ ሀብቶች ድንበር ተሻጋሪ ከመሆናቸው አንፃር ጠንካራ ዲፕሎማሲን ለመገንባት ጠንካራ ተቋም ለመገንባት እንቅስቃሴ ተጀምሯል ብለዋል፤ ኢትዮጵያ ያላትን የውሃ ሀብት ለዓለም ማሳወቅ ከዩኒቨርሲቲዎች ባለፈ የብዙ ሰዎች ድርሻና ኃላፊነት ነው ብለዋል።

መረጃውን ወደ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማድረስ የሚዲያው ዘርፍ ትልቅ ሚና ሊጫወት እንደሚገባ እና ጋዜጠኞች በትኩረት መሥራት መቻል እንዳለባቸው ተናግረዋል።

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ዶክተር ቦጋለ ገብረማርያም በበኩላቸው፤ በውሃ ሀብት ዙሪያ የተሠሩ ጥናቶች ተበታትነው እንደሚገኙ ጠቅሰው፤ ጥናቶቹን በአንድ ቦታ ማሰባሰብ ይገባል። ጥናቶቹ ምሁራን ውይይት ሊያደርጉባቸው እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

በዚህም አዳዲስ እውቀቶችን እና ግኝቶችን ማበልጸግና ማውጣት ይቻላል ያሉት ዶክተር ቦጋለ፤ ይህም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ያደርጋል ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ አብዛኛውን ጊዜ በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ግጭቶች ይኖራሉ። ግጭቶቹን ለማስቀረት የውይይት መድረኮች ይዘጋጃሉ። በመድረኮች አሳማኝ ሃሳቦች መቅረብ አለባቸው። አሳማኝ ሃሳቦቹ ከምርምር ይገኛሉ። ከድርድር በፊት ምርምሮች መደረግ ይኖርባቸዋል።

ኢትዮጵያ ውሃን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ትጠቀማለች እንጂ የግብፅ ሕዝብ ላይ ጫና ለማሳደር ፍላጎት የላትም ብለዋል፤ ይህን ጉዳይ ለዓለም ሕዝብ ለማሳየት የተማረና ሰዎች በሚገባቸው ቋንቋ ማስረዳት የሚችል ብቁ ዜጋ አስፈላጊ ነው። ይህን ማሟላት የሚችል ወጥ ተቋም ለመገንባት እየተሠራ ነው።

ይህም ለሀገሪቱ ዲፕሎማሲ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ገልጸው፤ መርህን መሠረት ያደረገ ሳይንሳዊ ምርምር በማድረግ በሀገር ደረጃ ተጠቃሚነትን ለማምጣት የውሃ ሀብት ዲፕሎማሲ ፎረም እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል።

# በክልሉ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የተሻሻሉ እንስሳት ዝርያዎች ለአርሶ አደሩ ተሰራጭተዋል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**



አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የተሻሹሉ እንስሳት ዝርያዎችን ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ማድረግ መቻሉ ተገለጸ።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊና የእንስሳት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ቶሌራ ደበላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በበጀት ዓመቱ 523 ሺህ የተሻሻሉ የቤት የእንስሳትን ለአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ እንዲደርሱ ተደርጓል።

ከተሻሻሉ ዝርያዎች የሚወለዱ ጥጃዎችን ቁጥር 223 ሺህ ደርሷል ያሉት ኃላፊው፤ በመጪዎቹ ወራት ቁጥሩ ከዚህ እንደሚጨምር ጠቁመዋል። ከዚሁ በተጓዳኝ በተለያዩ አካባቢዎች የተሠራው ከብቶች የማደለብ ሥራ ውጤታማ እንደነበርም በመግለጽ፤ ክልሉ ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ያለው በመሆኑ እየተመዘገበ ያለው እድገት ከአርሶ አደሩ ባለፈ ሀገራዊ ፋይዳ እንደሚኖረውም አስረድተዋል።

እንደ አቶ ቶሌራ ማብራሪያ፤ በክልሉ ስምንት ዞኖች ላለፉት ሦስት ዓመታት ተከስቶ የነበረው ድርቅ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎ ነበር። በአንጻሩ በ2015 በጀት ዓመት የበልግ ዝናብ እና ለቆላማ አካባቢ የክረምት ዝናብ ከሚያዚያ አጋማሽ ጀምሮ በስፋት በመጣሉ እድሉን በመጠቀም ለእንስሳት መኖ ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራ ቆይቷል። ከዚህም በተጨማሪ ድርቅ በተደጋገመባቸው አካባቢዎች 715 ሺህ ሄክታር መሬት ለመስኖ ልማት ማዋል የተቻለ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ሳር እየታጨደ ለእንስሳት ምርት እየተሰበሰበ ይገኛል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍም በተለያዩ ቦታዎች የውሃ ጉድጓዶች እየተዘጋጁ ይገኛል። ከእነዚህም ውስጥ በቦረና አካባቢ ብቻ 18 ትልልቅ ኩሬዎች የተገነቡ ሲሆን፤ ከእነዚህ የሚገኘው ከ20 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ በላይ ውሃ ለመስኖ፤ ለእንስሳት መጠጥና መኖ ልማት የሚውሉ ይሆናል።

በእንስሳት እርባታ ዘርፍ እንደ ችግር የሚነሳው የእንስሳት በሽታ መሆኑን ያስታወሱት ኃላፊው፤ ይህንንም ለመከላከል በክልሉ በአራት ቦታዎች የእንስሳት ላቦራቶሪዎች በሙሉ አቅማቸው እየሠሩ ይገኛል። በሰው ሀብት ረገድም ከቀበሌ ጀምሮ ያሉ የእንስሳት ሕክምና ባለሙያዎችን በመጠቀም እየተሠራ ሲሆን፤ የግብአት አቅርቦትን በፍጥነት ተደራሽ ለማድረግም በየአካባቢው የሕክምና ግብአት ማስቀመጫ መጋዘኖች መዘጋጀታቸውን አብራርተዋል።

በክልሉ በዶሮ እርባታ ረገድ በተሠራው ሥራ 18 ሚሊዮን የአንድ ቀን ጫጩት ለማቅረብ እቅድ ተይዞ ወደ ሥራ የተገባ መሆኑን አያይዘው ያነሱት አቶ ቶሌራ፤ ሥራውን በእቅዱ መሠረት ማከናወን መቻሉን ተናግረዋል። በተመሳሳይ 11 ሚሊዮን ቄብ ዶሮዎችን ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ ታቅዶ ሦስት ጊዜ ክትባት የተሰጣቸው 13 ሚሊዮን ቄብ ዶሮዎችን ተደራሽ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

በንብ ማነብም ረገድ በ15 ዞኖች በሚገኙ ለዚሁ ሥራ በተለያዩ አካባቢዎቸ 325 ሺህ ዘመናዊ ቀፎዎችን ተደራሽ ለማድረግ ታስቦ በተሠራው ተጨማሪ ሥራ 357 ሺህ ማድረስ የተቻለ ሲሆን፤ እንደ ክልል የነበረው የማር ምርትም እየጨመረ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሰላም ዋጋ መክፈል ለሀገርና ለሕዝብ ተቆርቋሪነት ዋነኛ መገለጫ ነው

ለአንድ ሀገር ህልውና ሆነ ሁለንተናዊ እድገት፤ ሰላም መሠረታዊ ጉዳይ ስለመሆኑ ብዙ ነጋሪ የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም። ይህንን ተጨባጭ እውነታ ታሳቢ በማድረግም ሀገራት ለሰላም ከፍያለ ትኩረት ሰጥተው ይንቀሳቀሳሉ። ለሰላም ቀናኢ ትውልድ ከማፍራት ጀምሮ፤ሰላምን አጽንተው መሄድ የሚያስችሉ ጠንካራ ተቋማትን ለመገንባት ብዙ ርቀት ይጓዛሉ።

በዚህም ሂደት/ጥረት የተሳካላቸው የዓለም ሀገራት ሕዝቦች እያንዳንዷን ቀን በሰላም፤ ከሰላም በሚመነጭ መንፈሳዊ እና አእምሯዊ መረጋጋት መምራት የሚያስችል ማኅበረሰባዊ/ ሀገራዊ ሥነልቦና መፍጠር የሚያስችል አቅም ፈጥሮላቸዋል፤ የጠንካራ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ሕይወት ባለቤት መሆን የሚያስችላቸውን ቁመናም አላብሷቸዋል።

እነዚህ ሀገራት ዜጎቻቸው ስለ ሰላም ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨብጡ፤ በእያንዳንዱ ዜጋ የሕይወት ትርክቱ ውስጥ የሰላም ጉዳይ ተገቢውን ስፍራ እንዲያገኝ፤ መንፈሳዊ ፣ ማኅበራዊ እና ባህላዊ መስተጋብሮቹ ለሰላም ሁለንተናዊ አቅም ሊሆኑ የሚችሉበትን የማኅበረሰብ መስተጋብር ፈጥረው ከትውልድ ትውልድ ማስቀጠል የሚችል ሥርዓት ገንብተዋል።

በየዘመኑ ያለው ትውልድ የዛሬ ማንነቱ ሆነ አሁን ላይ እንደሀገር /ማኅበረሰብ የደረሱበት ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ስኬት የሰላማቸው ትሩፋት መሆኑን በአግባቡ እንዲረዳ በማድረግ፤ ሰላሙን አጥብቆ እንዲጠብቅ የሚያስችል ጠንካራ የአዕምሮ መዋቅር መፍጠር ችለዋል። ለዚህም በየደረጃው ያሉ የትምህርት ሥርዓቶችን አቅም መገንቢያ ስትራቴጂክ መሣሪያ አድርገው ተጠቅመውበታል።

በእነዚህ ሀገራት የሚገኙ የጸጥታና የፍትሕ አካላትም ቢሆኑ ገና ከጅምሩ በዚህ እውነታ በተገነባ የአስተሳሰብ መሠረት ላይ የተዋቀሩ በመሆናቸው ውጤታማ መሆን ችለዋል። እራሳቸውን ከዘመኑ ጋር ተለዋዋጭ ከሆነው ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ እውነታ ጋር አስተሳስረው በመሄዳቸውም ጥንካሬያቸው ሳይሸረሸር ከትውልድ ትውልድ መሻገር ችለዋል።

በኛም ሀገር ድህነትን ታሪክ እናደርጋለን በሚል በለውጡ ማግስት የተጀመረው ሀገራዊ ንቅናቄ ስኬታማ እንዲሆን የለውጡ ኃይል ከሁሉም በላይ ለሰላም ከፍያለ ትኩረት ሰጥቶ ተንቀሳቅሷል። ችግሮችን በይቅርታ ከማለፍ ጀምሮ፤ አለመግባባቶችን በሃሳብ የበላይነት በውይይት ለመፍታት የሚያስችሉ አማራጮችን ይዞ በመምጣት ሀገሪቱን ከግጭት አዙሪት ለማውጣት ሞክሯል።

በታሪክ ካለፍንባቸው የኃይል እና የሴራ ፖለቲካ አንጻር ጥረቶቹ የተፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት አልቻሉም። ከሁሉም ይልቅ የሰላም እጦት በየዘመኑ ካስከፈለን አስከፊ ዋጋ አለመማራችን እንደ ሀገር ተፈጥሮ የነበረውን መልካም አጋጣሚ መጠቀም እንዳንችል በፍጥነት ውጤታማ እንዳናደርገው አድርጎናል።

በዚህም ከድህነታች ፣ ከኋላ ቀርነታችን ከዚህም ባለፈ ዛሬ ላይ ዋጋ እያስከፈሉን ካሉ ችግሮቻችን በስተጀርባ ያለው ስለ ሰላም ያለን የተዛባ አመለካከታችን መሆኑን በፖለቲካችን ውስጥ ያለው ፉከራና ቀረርቷችን ፣ ከዚህ የሚመነጨው ጀብደኝነታችን እንደ ሀገር ዛሬያችንን ብቻ ሳይሆን ነገዎቻችንን ጭምር እየገደሉብን ስለመሆናቸው ማስተዋል አልቻልንም።

አሁን ላይ በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች ተስፋ ያደረጉት ድህነትን ታሪክ የማድረግ ህልም እውን ማድረግ የሚችለው ከሁሉም በላይ ስለ ሰላም ያለን የተዛባ አመለካከት ሲለወጥና በተለወጠው አመለካከት የተገነባ ሀገራዊ ሥነልቦና መፍጠር ስንችል ነው። ከዛ ውጪ "ውረድ እንውረድ" በሚለው ዘመን ያለፈበት ሀገርን በጎዳ ዜማ ድህነትን ታሪክ ማድረግ አንችልም።

ለሀገርና ለሕዝብ ተቆርቋሪ ነኝ የሚል የትኛውም ግለሰብ ሆነ ቡድን ስለ ሰላም ያለውን የተዛባ አመለካከት ሊያርም ይገባል። እንደ ሀገር የሰላም ማጣት ያስከፈለንን ያልተገባ ዋጋ ቆሞ በማጤን፤ ስለ ሰላም ሊከፈል የሚገባውን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል ዝግጁነትን መፍጠር ይጠበቅበታል፤ ለሀገርና ለሕዝብ ተቆርቋሪነት ዋነኛ መገለጫውም ይኸው ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## እየተባባሰ የመጣው የአየር ንብረት ለውጥ

ግርማ መንግሥቴ

ከአላርም (አጣዳፊ የድረሱልኝ ጥሪ) በስተቀር በዚህ ጽሑፍ ምንም አዲስ ነገር ይዘን አልመጣንም። ጉዳዩ የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ሆነና ነው እንጂ፣ በችግሩ ዙሪያ ያልተባለ ነገር የለም።

በዓለማችን የችግሩ መኖር ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በአየር ጸባይ ለውጥ ዙሪያ ያልተካሄደ ስብሰባ፤ ያልመከረ ጉባዔ፣ ያልተፈረመ ስምምነት አለ ለማለት በማይቻል ደረጃ ሀገራት በመሪዎቻቸው አማካኝነት መክረዋል፤ ዘክረዋል፤ ምለው ተገዝተዋል።

በዘርፉ ያልተካሄዱ የጥናትና ምርምር ሥራዎች እንደሌሉ ሁሉ ያልተረቀቁ ፖሊሲዎችና ያልወጡ ሕጎችም የሉም። ይህ ሁሉ ይሁን እንጂ፣ የችግሩ ቀስት ዛሬም ወደ ላይ እንጂ ወደ ታች ሲያመለክት አይታይም።

የግላስኮው ኮፐ26 የአየር ንብረት ጉባኤ፣ የፓሪስ ስምምነት ወዘተ ሁሉ ይህንኑ የአየር ንብረት ለውጥን ለመታደግ የተደረጉ ውይይቶችና ስምምነቶች ናቸው፤ ከራሱ ከተባበሩት መንግሥታት ጀምሮ፣ ግሪን ፒስንና የመሳሰሉትን ይዞ በርካታ ድርጅቶች በዚሁ ችግር ዙሪያ በሥራ ተጠምደናል የሚሉ አካላት ናቸው። እነሱ ይህንን ይበሉ እንጂ ዓለም በየቀኑ እየነፈረች ከመሄድ ወደ ኋላ ያለችበት ደቂቃ የለም።

ያደጉት ሀገራት በአውሮፓውያኑ 2009 ደሃ ሀገራትን ለመደገፍና አማራጭ የኃይል መንገዶችን ለመደገፍ እስከ 100 ቢሊዮን ዶላር ድረስ ፈሰስ ለማድረግ ቃል ገብተው እንደነበር ይታወሳል። ቃል ይግቡ እንጂ እስካሁን ምንም የለም።

የዘርፉ ተመራማሪዎች በተደጋጋሚ እንደሚሉት፣ ያደጉት ሀገራት የገቡትን ቃል ለመፈጸም ቸልተኝነት ባሳዩ ቁጥር ከባድና ተደጋጋሚ ጎርፎች፣ በረሃማነት እንዲሁም ያልተለመደ ቅዝቃዜ እየጨመረ ይሄዳል። ይህም ለዓለማችን እጅግ አስጊና አጥፊ ነው። በመሆኑም ቃል የተገባው መፈፀም አለበት።

ወዳለንበት፣ ወደ ወቅታዊው የዓለማችን ሁኔታ እንምጣ፤ "የአየር ንብረት" ማለት በአንድ ሥፍራ ያለው የአየር ፀባይ በዓመታት የሚያሳየው አማካይ ውጤት፤ "የአየር ንብረት ለውጥ" ደግሞ የዚህ አማካይ አየር ፀባይ መቀየር ማለት መሆኑን ልብ ይሏል።

የቻይናን እና የሩሲያ መሪዎች ያልተገኙበት፤ በዓለማችን ከፍተኛውን የካርቦንዳይኦክሳይድ ልቀት የሚያደርጉት አሜሪካ እና ቻይና በሚቀጥሉት አስር ዓመታት በአየር ጸባይ ለውጥ ዙሪያ (ለግሪንሃውስ መሸንቆር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርገውን የሚቴን ልቀት፣ ወደ ንጹህ ኃይል መሸጋገር እና ካርቦንን ማጥፋትን ጨምሮ) ተባብረው ለመሥራት መስማማታቸውን ይፋ አድርገዋል።

የቻይና ከፍተኛ የአየር ንብረት ተደራዳሪ የሆኑት ዢ ዤንሁዋ "በቻይና እና አሜሪካ መካከል ካለው ልዩነት በበለጠ ስምምነት አለ" በማለት የተናገሩበት የግላስጎው የአየር ጸባይ ስምምነት የከሰል ምርትን ከመቀነስም ባለፈ ሙሉ ለሙሉ ለማስቀረት የሚያስች የውሳኝ ሃሳብ የቀረበበት ነበር ።

በወቅቱ የከሰል ምርትን ሙሉ ለሙሉ ለማስቀረት የቀረበውን ሃሳብ የሕንዱ የአየር ንብረት ሚኒስትር ብሁፔንደር ያዳቭ በስብሰባው ወቅት "ድሃ ሀገራት ድህነትን ለመቀነስና የእድገት ጎዳናቸውን ለማሳለጥ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዴት አድርገው ከከሰል ሌላ አማራጭ ኃይል መጠቀም ይችላሉ?" በሚል ተቃውሞ አሰምተው ፤ በኋላም ሃሳባቸው ተቀባይነት አግኝቶ ውሳኔው ወደ "ቀስ በቀስ መቀነስ..." መሻሻሉ ይታወሳል።

በወቅቱ የተደረሰበት ስምምነት በአይነቱ የመጀመሪያ የተባለለት መባሉም ይታወሳል። ስምምነቱ ጎጂ ጋዞችን መልቀቅ በፍጥነት እንዲቆም ወስኖ የነበረ መሆኑም እንደዛው። ግን፣ "ምን ለውጥ መጣ?" እንደ ባለሙያዎቹ እይታ ከሆነ "ምንም"።

ፖላንድ፣ ቬትናም እና ቺሊን ጨምሮ ዋና ዋና የከሰል ተጠቃሚዎች እንደ ከሰል፣ ፔትሮሊየምና የተፈጥሮ ጋዝ የኃይል ምንጮችን ላለመጠቀም ቃል የገቡበት፤ ፖላንድ፣ ቬትናም እና ቺሊ ለመጀመሪያ ጊዜ የድንጋይ ከሰል ኃይል ላለመገንባት እና በዘርፉ መዋለ ንዋይ ላለማፍሰስ ከተስማሙ 18 ሀገራት መካከል መሆናቸው በደስታ የተገለፀበት ነበር ።

የቀድሞው የዩኤስ አሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ወጣቶችን ለአየር ንብረት ለውጥ "ተነሱ!!!" በማለት ጥሪ ያስተላለፉበት ... የግላስጎው ኮፐ26 የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ ምን ላይ ደረሰ??? ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው መልስ ወደ ኋላ የሚወስድ እንጂ ወደ ፊት የሚያራምድ አይደለም፤

ችግሩ "የሰዎችንና የተፈጥሮ ሀብትን ህልውና እየተገዳደረው ይገኛል" ከሚለው ማእቀፍ ውስጥ አልወጣም። ወይም፣ ወፎች ሳይቀሩ ከሀገር ሀገር እየተሰደዱ ከመጥፋት የታደጋቸው አካል የለምና በጉዳዩ ላይ ተሰርቷል ለማለት አይቻልም።

ተመራማሪዎቹ እንደሚናገሩት ከሆነ፣ የዓለም ሙቀት ከ 1.5 ሴልሺየስ በላይ ከፍ የሚል ከሆነ ምድራችን አይታው የማታውቀው አይነት ቀውስን ታስተናግዳለች። በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ሰዎችም ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ይወድቃሉ። በኮፐ26 ጉባኤ ላይ እንደተገለፀው፤

- የሙቀት መጠን 1.5 ሴልሺዬስ ላይ መቆየት ካልቻለ ምድረ አውሮፓ በጎርፍ ልትጥለቀለቅ ትችላለች፤
- የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ከፍተኛ ሙቀት ያስተናግዳሉ፤ የእርሻ ቦታዎች ወደ በረሃማነት ይቀየራሉ፤
- የውቅያኖስ መጠን ሲጨምር በፓሲፊክ ክፍል ያሉ ደሴቶች የሚዋጡበት እድል ይኖራል፤
- በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ድርቅ ያጠቃቸዋል፤ የምግብ እጥረት ያጋጥማቸዋል፤
- ምዕራባዊ የአሜሪካ ክፍል በድርቅ ሲጠቃ፤ የተቀረው ክፍል ደግሞ በነጎድጓድ ዝናብ የመጥለቅለቅ አደጋ ይገጥመዋል፤
- አውስትራሊያ በከባድ ድርቅና ሙቀት ልትጠቃ የምትችልበት እድል ሰፊ ነው።

ተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በኮፐ26 የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ ላይ "በአየር ንብረት ለውጥ የሚመጣ ትልቅ ቀውስ እንዲከሰት እያደረግን ነው። በፍጥነት ውሳኔ ላይ ደርሰን ምድራችንን የምንታደግበት ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ደርሰናል" በማለት እንዲናገሩ፤ የችግሩንም ጣራ መንካት እንዲገልፁ አስገድዷቸዋል።

ያ እንዳለ ሆኖ፣ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በቅርቡ የዓለም ሳይንቲስቶች አጥንተው ያቀረቡላቸውን የአየር ንብረት ለውጥ ሪፖርት መነሻ አድርገው የዓለማችን መልካም ጊዜ እያለፈ፤ የዓለማችን መጥፊያ ወቅት በፍጥነት እየመጣ ነው። በመሆኑም ያለ ምንም ጊዜ ማጥፋት መሪዎች በዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ትኩረት ሰጥተው ሊሠሩ ይገባል በማለት ገልፀዋል።

እርግጥ ነው፣ የአየር ንብረት ለውጥ በከፍተኛ ደረጃ እየታየ ነው። ለዚህ ምክንያቶቹ ቢለያዩም በአብዛኛው የሰው ልጅ ራሱ የሚያደርሰው ጥፋት ስለ መሆኑ ሁሌም በማስረጃ ተደግፎ እየቀረበ ይገኛል። በተለይ ባለሀብት ተብዬ ግዙፍ ኩባንያዎች ማእድን አለ፣ ነዳጅ እናወጣለን ... በማለት ደን ምንጠራውን ሊያቆሙ ይገባል።

የዓለም ሳይንቲስቶች "የምድራችንን ሳንባዎች ጠብቁ" ምክር ካልተሰማ፤ በካይ ጋዞችን የመቀነስ ሥራዎች ካልተሰሩና ሌሎች ችግሮችም ካልተወገዱ (ከፍተኛ ሙቀት እና ሰደድ እሳት ጉዳት ሲያደርስ ከባድ ዝናብ ባመጣው ጎርፍም የሰዎች ሕይወት እና ንብረት ሲጠፋ እየተመለከትን መሆኑን ልብ ይሏል) ዓለማችን የሚጠብቃት አደጋ ግልፅ ነው።

ከላይ ለደንቡ ያህል የገለፅናቸው እንዳሉ ሆነው፣ እጅግ አሳሳቢው የሰሞኑ የሳይንቲስቶቹ ሪፖርት ሙሉ ተቀባይነትን አግኝቶ ሁሉም በችግሩ ላይ እጁን ሊያነሳ ይገባል።

# ተቋርጦ የነበረው የሕዳሴ ግድብ የሦስትዮሽ ድርድር በካይሮ ተጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ተቋርጦ የነበረው የሕዳሴ ግድብ የሦስትዮሽ ድርድር በትናንትናው ዕለት በግብፅ ካይሮ ተጀምሯል።

ኢትዮጵያ በድንበር ተሻጋሪው ዓባይ ወንዝ ላይ እየገነባችው ያለው ታላቁ የሕዳሴ ግድብ የሦስትዮሽ ድርድር በተለያዩ ምክንያቶች መቋረጡ ይታወሳል።

ይሁንና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ በግብፅ ባደረጉት ጉብኝት፤ ከሀገሪቱ ፕሬዚዳንት አብደልፈታህ አልሲሲ ጋር በደረሱት ስምምነት መሠረት የሦስትዮሽ ድርድሩ ዳግም መጀመሩ ነው የተገለጸው፡፡

በዚህም ረቂቅ ስምምነቱ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ውይይትና ድርድር እንደሚደረግ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መረጃ ያመላክታል፡፡

ድርድሩ የኢትዮጵያን ተጠቃሚነት እና የወደፊት የመልማት መብት ባስከበረ መልኩ ለማካሄድ አስፈላጊው ዝግጅት መከናወኑም ተገልጿል፡፡

አምባሳደር ዶ/ር ስለሺ በቀለ በሚኒስቴር ማዕረግ የኢትዮጵያ ተደራዳሪ ቡድን መሪ በመክፈቻ ንግግራቸው፤ ይህ የሦስትዮሽ ድርድር በሦስቱ ሀገሮች መካከል ትብብርን ለማጠናከር የሚረዳ መሆኑን ገልጸው፤ የኢትዮጵያ የአሁኑንና የወደፊት ትውልድ ጥቅም ለማስጠበቅ በዓባይ ውሃ የመጠቀም መብት መሠረታዊ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡

ግድቡ ለሦስቱ ሀገራት የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ መሆኑን የገለጹት አምባሳደር ዶ/ር ስለሺ፤ ኢትዮጵያ በፍትሐዊና ምክንያታዊ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሠረተ አቋሟን አጠናክራ ድርድሩ በመግባባት እንዲጠናቀቅ እንደምትሠራ ገልጸዋል፡፡

# ባለሥልጣኑ 700 የሚጠጉ አዳዲስ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን መዘገበ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የኢፌዴሪ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን 700 የሚጠጉ አዳዲስ የሲቪል ማኅበር ድርጅቶችን መመዝገቡን አስታወቀ። ሦስት ሺህ 300 ድርጅቶች ላይ የቁጥጥር ሥራ ሠርቷል፡፡

የኢፌዴሪ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ፋሲካው ሞላ እንደገለጹት፤ ተቋሙ ተቋማትን መመዝገብ፤ እውቅና መስጠት እና ምዝገባ ያከናወነባቸው ድርጅቶችን መቆጣጠር ዋና ዋና ሥራዎቹ እንደመሆናቸው መጠን አዳዲስ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን መዝግቧል፡፡ በዚህም በበጀት ዓመቱ ተቋሙ ከዚህ ቀደም የመዘገባቸው ሦስት ሺህ 300 የሚሆኑ ድርጅቶች ላይ ቁጥጥር ያደረገ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥም ከሁለት ሺህ በላይ ለሚሆኑት ድርጅቶች ክፍተታቸውን እንዲያውቁና እንዲያስተካክሉ ተደርጓል።



**አቶ ፋሲካው ሞላ**

ተቋሙ የምዝገባ ሥርዓቱን ቀላልና ቀልጣፋ በማድረግ በ2015 በጀት ዓመት 688 የሚሆኑ አዳዲስ ድርጅቶችን መመዝገብ ተችሏል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በአዲስ መልክ ከተመዘገቡት ድርጅቶች ውስጥ 634 የሚሆኑት ሀገር በቀል መሆናቸውንና 54 የሚሆኑት ደግሞ የውጪ ድርጅቶች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸርም የተሻለ ቁጥር ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

አቶ ፋሲካው፤ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለተቋቋሙበት ዓላማ እና የሕዝብ ጥቅምን ባማከለ መልኩ በሕግ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል ሲሉ ገልጸው፤ ተቋሙም ሕግን ተከትለው የማይሠሩ ድርጅቶች የመስክ ቁጥጥር ማድረጉን አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል።

የተቋሙን አቅም የመገንባትና ቅንጅታዊ አሠራርን ይበልጥ የማስፋት ሥራ ሲሠራ ቆይቷል ያሉት አቶ ፋሲካው፤ በዚህም ተቋሙ የመፈጸም ማስፈጸም ሥራውን በአግባቡ ተወጥቷል፡፡ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ለተገልጋዮች ለማቅረብ የዲጂታል ሲስተም በመዘርጋት የተለያዩ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል። ከዛ ባሻገር ከተለያዩ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ጋር በመሆን የቅንጅት ሥራ የተሠራበት ዓመት ነው። ለዚህም ማሳያ የሚሆነው የተገልጋዮችን የአገልግሎት እርካታ 92 በመቶ ማድረስ መቻሉ ነው። ይህም ከባለፉት የሪፎርም ዓመታት ጋር ሲታይ ጥሩ መሻሻል እያሳየ የመጣ ነው ብለዋል፡፡

ሌላኛው በዚህ ዓመት ከተሠሩ ዋነኛ ሥራዎች መካከል ዘላቂ ሰላም ለማምጣት መንግሥት በሚሰራቸዎ ሥራዎች ንቁ ተሳትፎ ነው ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዚህም በትግራይ ክልል የሚንቀሳቀሱ ሁሉንም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በመሰብሰብ አዲስ በወጣው መመሪያና አዋጅ ዙሪያ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

አሁን ባለው የሰላም ሁኔታም በክልሉ የሚገኙ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ሪፖርት በማሰባሰብ የሚደረገው ድጋፍ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል፡፡

# የሀገሪቱን ሁለንተናዊ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኢንስቲትዩቱ 73 ያህል የጎረቤት ሀገራት ዜጎች አሠልጥኖ ማስመረቁ ኢትዮጵያ ለምትከተለው ከጎረቤት ጋር አብሮ የማደግ ፖሊሲ ማሳያ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ ዘርፉ ያለውን እምቅ አቅም ለማውጣት የሚሆን ክህሎትና እውቀትን ያገናዘበ ሥልጠና መውሰድ ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ እድገት አስፈላጊ ነው፡፡

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ከድር (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ሀገሪቱ የጀመረችውን ለውጥ ለማረጋገጥ በእውቀት በክህሎት እንዲሁም ችግር ፈቺ እንዲሁም ሙያውንና ሀገሩን የሚወድ ዜጋ ማፍራት አስፈላጊ በመሆኑ ቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ጠቀሜታ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

እንደ ዶክተር ብሩክ ገለጻ፤ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ሀገሪቱ ለምትከተላቸው የለውጥ ተግባራት የሚደግፍ ነው፡፡ ቀጣናዊ ትስስርን ለማጠናከር ከደቡብ ሱዳንና ሶማሌ ላንድ 253 ሠልጣኞችን ዕለት ተቀብሎ 73 የሚሆኑትም በትናንትናው ዕለት ተመርቀዋል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የሀገሪቱን የልማት ፖሊሲዎች የተከተለና ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድግ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ልማት ሥራዎች የሚያበረታታ ነው ያሉት ዶክተር ብሩክ፤ ኢንስቲትዩቱ ሠልጣኞችን የመቀበል አቅም በማሳደግ ሥልጠናው እስከ ደረጃ ስምንት ድረስ ለመስጠት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ከተመራቂዎች መካከል ሁለት ሺህ 786 የሚሆኑት በመጀመሪያ ዲግሪ ሲሆን፤ ስምንት መቶ 65 በሁለተኛ ዲግሪ ተመርቀዋል፡፡

በኢንስቲትዩቱ የተመረቁት ተማሪዎች በመካኒካል ቴክኖሎጂ፣ በሲቪል ቴክኖሎጂ፣ በኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክስ፣ በአይሲቲ፣ ቴክስታይልና ጋርመንት እንዲሁም በአግሮ ፕሮሰሲንግ ዘርፍ የሠለጠኑ ናቸው፡፡

# የጤና ኤክስቴሽን መርሀ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ 16 ሺህ 895 ጤና ኬላዎች በፍኖተ ካርታው መሠረት መለየታቸው ተጠቁሟል።

በጤና ሚኒስቴር የማኅበረሰብ ተሳትፎና የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ዴስክ ኃላፊ አቶ ወንድወሰን ንጋቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የኅብረተሰቡን ጤና በመጠበቅና በሽታን ቀድሞ በመከላከል ላይ ትኩረት በማድረግ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተተገበረ ይገኛል፡፡

ፕሮግራሙ የቤተሰብ ጤና፣ በሽታን መከላከል፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅና የጤና ትምህርት የሚሉ አራት ዋና ዋና ክፍሎች እንዳሉት አስረድተዋል።

ክትባት፣ የወሊድ ክትትል አገልግሎትና የቤተሰብ ምጣኔ ዕቅድ በቤተሰብ ጤና ላይ የሚተገበሩ ሲሆን፤ በሽታን በመከላከል ደግሞ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እንደ ቲቪ፣ ኤች አይቪ ኤድስ፣ ወባና ሌሎች በሽታዎችን የመከላከል ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአካባቢ ጤና አጠባበቅ ላይ የመጸዳጃ ቤት፣ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ የእንስሳት መኖሪያን ከሰው መኖሪያ መለየት እና ሌሎችም እየተተገበሩ ሲሆን፤ 18 ጥቅሎችን የያዘ የጤና ትግበራዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ለኅብረተሰቡ የጤና ትምህርት እና ግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠቱን አስታውቀዋል፡፡

በዚህም በእናቶችና ሕፃናት ሞት ቅነሳ፣ በሽታን በመከላከል እና ተላላፊ በሽታዎችን በመቀነስ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል ብለዋል፡፡

ከፕሮግራሙ ጋር በተያያዘ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ለ15 ዓመት የሚተገበር የጤና ኤክስቴንሽን ማሻሻያ ፍኖተ ካርታ ተግባራዊ መደረግ መጀመሩን አመላክተዋል።

የኅብረተሰቡን ጤና ከማጎልበትና በሽታን ከመከላከል ጎን ለጎን አንዳንድ አገልግሎቶች ወደ ጤና ኬላ እንዲወርዱ ከኅብረተሰቡ በተነሳው አስተያየት መሠረት በሥራ ላይ ያሉ ጤና ኬላዎችን አጠቃላይ፣ መሠረታዊ እንዲሁም ጤና ኬላ ተብለው እንዲከፈሉ መደረጉን ጠቁመዋል።

ትግራይ ክልልንና አንዳንድ የጸጥታ ችግር ያለባቸው አካባቢዎች ሳይጨምር 16 ሺህ 898 ጤና ኬላዎች በፍኖተ ካርታው መለየታቸውን ገልጸዋል።

በዚህም መሠረት አንድ ሺህ 873 አጠቃላይ ጤና ኬላ፣ 12 ሺህ 470 መሠረታዊ ጤና እንዲሁም ሁለት ሺህ 555ቱ ደግሞ ከጤና ጣቢያ በመባል እንዲለዩ መደረጉን አብራርተዋል፡፡

አጠቃላይ ጤና ኬላ ከጤና ተቋማት ርቀት ላይ ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት እንዲያገኙ የሚረዳ ሲሆን፤ ሁለት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ፣ ጤና መኮንን፣ አዋላጅ ባለሙያ፣ ፋርማሲስት እና የላቦራቶሪ ባለሙያ ተመድበው ለኅብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጡበት መሆኑን አስረድተዋል።

መሠረታዊ ጤና ኬላ ደግሞ 18ቱ ጥቅሎች ላይ ትኩረት አድርጎ ማኅበረሰቦች እስከ አንድ ሰዓት በእግር ተጉዘው አገልግሎት የሚያገኙበት ሲሆን፤ ሁለት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችንና አንድ ነርስ የሚመደቡበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የጤና ኬላዎችን መሠረተ ልማት በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መቀየር፣ ፍኖተ ካርታውን በሚፈለገው ደረጃ በመተግበር፣ የባለሙያዎችን አቅም ማጎልበትና ለኅብረተሰቡ ጥራት ያለው እና ተደራሽ የሆነ አገልግሎት መስጠት የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እገዛ ማድረግ እንዳለባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

# ስለ ዓይን ባንክ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሚል በአዲስ መልክ ተደራጅቶ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ አንስተዋል።

ተቋሙ ከለጋሾች የዓይን ብሌን በመሰብሰብና በማዘጋጀት በሀገሪቱ ባሉ የተለያዩ የንቅለ ተከላ ተቋማት በማሰራጨት በዓይን ብሌን ጠባሳ ምክንያት ብርሃናቸውን ላጡ ዜጎች ዳግም ብርሃናቸውን እንዲያገኙ የበኩሉን እየተወጣ ያለ ተቋም እንደሆነ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የዓይን ባንክ ሜዲካል ዳይሬክተር ዶክተር መነን አያሌው በበኩላቸው፤ ተቋሙ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ለሦስት ሺህ 75 ዜጎች የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ ያደረገ ሲሆን፤ ከ14 ሺህ በላይ ዜጎች ሕይወታቸው ሲያልፍ የዓይን ብሌናቸውን ለመለገስ ቃል መግባታቸውን አመላክተዋል።

በመላው ኢትዮጵያ 12 የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ ባለሙያዎች ተሰማርተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ ብለዋል። ለተቋሙ ድጋፍ ሲያደርጉ ለነበሩ ተቋማትና ግለሰቦች የእውቅናና የሽልማት መርሀ ግብርም ተከናውኗል።

የኢትዮጵያ የዓይን ባንክ ሰኔ 21 ቀን 1995 ዓ.ም የተመሰረተ ተቋም ነው።

## ነፃ ሃሳብ

# ፍቅር የሕግ ፍጻሜ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ለሰው ልጅ ለአብሮ መኖር መሠረት ከሆኑና አስቀድመው ከተነገሩ እውነቶች ውስጥ አንዱ ፍቅር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለፍቅር እና ስለዋጋው ብዙ መልዕክቶች ተጠቅሰዋል። ከዚህ ውስጥ አንዱ በሮሜ፣ በገላትያ፣ በኤፌሶን፣ እንዲሁም በሌሎች ምዕራፎች ላይ የምናገኘው ‹ፍቅር የሕግ ፍጻሜ› የሚለው ሃይለ ቃል ይጠቀሳል።

ፍቅር ከሌሎች ጋር አብሮ የሚያኖረን ተፈጥሮአዊ ሥርዓት ነው። ይሄ ሥርዓት በጥላቻ ካልሆነ በምንም እንዳይላላ ሆኖ የጸና የሕግ ፍጻሜ ነው። የሰው ልጅ ወደዚች ምድር ሲመጣ ከፍቅር ጋር ነው። ፍቅር ተፈጥሮአዊ የሰው ልጅ ማንነት ነው። ፍቅር የሕህግ ፍጻሜ ከተባለ ድህረ ዓለምም ሆነ ቅድመ ዓለም ሁሉም ኩነት በፍቅር ስርዐት ውስጥ እንደሆኑ መረዳት እንችላለን።

የሰው ልጅ ከጥላቻ ጋር ወይም ደግሞ ከተቃርኖ ጋር አልተፈጠረም። አፈጣጠራችንን ብናየው እንኳን ፈጣሪ በመልካችንና በአርአያችን የሰውን ልጅ እንፍጠር ብሎ እንደተነሳ የምንደርስበት እውነት አለ። እናም ወደዚች ዓለም በሰውነት ስንመጣ በፈጣሪ ሃሳብና ግብር ታንጸን ነው። የፈጣሪ ሃሳብ እና ግብር ደግሞ ፍቅር እና ፍቅር ብቻ ነው።

ሰውነት የፈጣሪ ሃሳብና ግብር የተዋሃዱበት ረቂቅ ማንነት ነው። በፈጣሪ ህልውና ውስጥ ደግሞ ፍቅር እንጂ፣ እውነት እንጂ ጥላቻና ሀሰት የለም። ይሄን እውነት የሚያረጋግጥ ሌላ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ መጥቀስ ቢያስፈልግ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 18 ማየት እንችላለን። በዚህ መልዕክት ላይ ‹እናተ የእግዚአብሄር ቤተመቅደሶች ናችሁ› ተብለናል።

ከዚህ እውነት በመነሳት የሰው ልጅ የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ እንደሆነ እንደርስበታለን። ቤተመቅደስ በባህሪው ቅዱስና ንጹህ ነው። በጎ ሃሳብና በጎ ምግባር የታጨቁበት ማንነት ነው። የሰው ልጅ ከፍቅር ጋር ብቻ ነው ወደዚች ዓለም የመጣው። ጥላቻና መሰል አላስፈላጊ ማንነቶችን የተማረው ሰው ከሆነ በኋላ ነው። ለዚህ የእውቁን የነጻነት ታጋይ የኒልሰን ማንዴላን ‹ፍቅር ተፈጥሮአዊ ነው ጥላቻ ግን በትምህርት የምናገኘው ነው› የሚለውን ዘመን ተሻጋሪ አባባል ማስታወስ ይቻላል።

የሀገራችን ፖለቲካ ጥላቻ ወለድ ፖለቲካ ስለመሆኑ ምስክር ሚያስፈልገው አይደለም ። ባልጸዳና ባልዘመነ ፖለቲካዊ ምህዳር የሥርዓት ሁሉ በኩር የሆነውን ፍቅርና አንድነታችንን ተነጥቀን ካብ ለካብ የሚተያዩ ባላንጣዎች ሆነናል። ብዙ ጥላቻዎችን እና የዘር እሳቤዎችን ወርሰን እርስ በርስ ስንገዳደልና ስንገፋፋ እንደነበር የአደባባይ ሀቅ ነው። አሁንም በዛ እውነት ውስጥ ነን።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ የሕዝብ ፖለቲካ አይደለም። የአንድ ቡድንና የአንድ ራስወዳድ ማንነት ሃሳብ እና ርዮት እንጂ። ፖለቲካችን ኢትዮጵያዊ መልክና ወዝ ቢኖረው ኖሮ በዚህ ልክ በጥላቻና በእኔነት ባልጎለመስን ነበር።

እንደኢትዮጵያዊነት እሴቶቻችን ብንኖር ጥላቻን የሚገል፣ መለያየትን የሚሽር እልፍ ሥርዓት ነበርን። እንደ ኢትዮጵያዊነት ብንኖር በጋራ የሚያቆም እልፍ የሥርዓትና የወግ እሴቶች ነበሩን። የፖለቲካው ሥርዓት ግን ያን እንድናደርግ እድል እየሰጠን አይደለም።

ጥላቻ ወለድ ፖለቲካ ሀገር አይሰራም። እንዲህ አይነቱ ለማንም የማይበጅ ሥርዓት ጥንተ በኩር ኢትዮጵያዊ ፍቅራችንን ካደበዘዘብን ሰንበትበት ብሏል። ፍቅር ያልነካው እውቀት፣ እውነት ያልገባበት ፖለቲካ በድህነት እና በኋላ ቀርነት ለሚሰቃይ ሕዝብ ንቃት አይሰጥም። ንቃታችን ያለው በፍቅር ውስጥ ነው። ፍቅር ከሚሉት የሥርዓት አውድ ፊት ቆመን በአንድነት ካልበላን፣ በአንድነት ካልተሰባሰብን የባሰ እንጂ የተሻለ አይመጣም።

ኢትዮጵያ የምትድነው ፖለቲካውም ፖለቲከኞቻችንም የሕዝብ ሲሆኑ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ይህን ማድረግ አንችልም። ኢትዮጵያዊነት ቀለሙ ፍቅርና አንድነት፣ ህብረት እና ወንድማማችነት ነው። ኢትዮጵያዊነት መሠረቱ ርህራሄና ቸርነት፣ ይቅርታና በጎነት ነው። ታዲያ ከኢትዮጵያ ጉያ በቅለው ኢትዮጵያን የማይመስሉት እነዚህ መልከ ልውጥ አእምሮና ልቦች ከየት መጡ?

> **ብሄራዊ ምክክር ብዙ ስም ቢኖረውም አንዱና ዋነኛው መገለጫው ግን የይቅርታ መድረክ የሚለው ነው። ፍቅር የሚመለሰው፣ አብሮነት የሚመጣው እንዲህ ባለው መነጋገርን ባስቀደመ ትውውቅ ነው። ይቅርታ ፍቅርን የሚያውቁ ሁሉ የሚናገሩት የነፍሶች ቋንቋ ነው። የይቅርታ ልብ ሁሌ ያማረ፣ ሁሌ የፈካ የፀሀይ መውጫ አናት ነው...በብርሃን የተሞላ። ይቅርታ ሳንሞት ህያው ሆነን በትውልድ ልብ ውስጥ የምንኖርበት ጥበባችን ነው**

በሕዝብ ፖለቲካ ውስጥ ጥላቻ የለም። እኔነት እና ወገኝተኝነት የተፈጠሩት ፖለቲካው ከኢትዮጵያዊነት ስለሸሸ ነው። ሀገር ያረቁ፣ ትውልድ ያቀኑ ባህሎቻችን የት ድረስ እንደሆኑ እናውቃለን። የእርቅና የአንድነት ሥርዓቶቻችን ፍትህና ዘመናዊነት ባልነገሡበት በዛ ዘመን ኢትዮጵያዊነትን አጽንተው ያራመዱ እንደነበሩ ለማንም የሚታወቅ ነው። በሸንጎና በጎሜ፣ በሽምግልናና በፈርሀ እግዚአብሄር ብዙ ጥላቻዎችን ወደፍቅር የቀየርን ሕዝቦች ነን።

ዛሬ ላይ መልካችን ተቀይሯል። ብዙ ባህልና ሥርዓት፣ ብዙ ወግና ልማድ ያላት ሀገር በጥላቻ ፖለቲካ ስትናጥ ማየት ብዙ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ ነው። ከዚህ እና ከመሰለው እውነታ በመነሳት የሚስፈልገን የሕዝብ ፖለቲካ ነው። የሕዝብ ፖለቲካ የአንድነት ፖለቲካ ነው። የሕዝብ ፖለቲካ ማንም የማይበድልበት፣ ማንም የማይበደልበት የፍትህና የሚዛናዊነት ፖለቲካ ነው።

ኢትዮጵያን ካንቀላፋችበት ለማንቃት የፍቅር ፖለቲካ ያስፈልገናል። ኢትዮጵያን አጎሳቁለን፣ ሕዝባችንን ተስፋ ቢስ አድርገን የምናተርፈው የብቻ ትርፍ የለም። በኢትዮጵያ ዝቅታ ውስጥ የሁላችንም ዝቅታ አለ። በከፍታዋም ከፍ የምንለው አብረን ነው።

ወላጆች በልጆቻችሁ ልብ ውስጥ ፍቅር ያለበትን ታላቅ ማንነትን መትከል ፤ የሀገር ፍቅርን፣ ሠብዓዊነትን፣ እውነትንና ሚዛናዊነትን ማውደስ ይጠበቅባቹኋል። መምህር ከሆናችሁ ለተማሪዎቻችሁ እውነትን፣ ይቅርታን ማስተማር ፤ በዚህም ጥሩ አርዐያ በመሆን ነጋቸውን መሥራት ይጠበቅባቹኋል። ከክፉ ሥራ ወጥተን በሚጠቅመንና በምንባረክበት ቅዱስ ሥፍራ ላይ መቆማችን ከዝቅታ የሚታደገን በኩረ ኃይላችን ነው።

አባቶቻችን ኢትዮጵያን አቀንጅተው ለዓለም ያስተዋወቁት በጥላቻና በመከፋፈል ሳይሆን በአንድነት እና በፍቅር ነበር። በቀና ልብ፣ በጽኑ ሀገር ወዳድነት፣ በፍቅር ብርሃን እንዳጠመቁን እኛም ለሌሎች የሚሆን ብዙ ፍቅርን፣ ብዙ ይቅርታን መላበስ ታሪክ የምንቀይርበት መነሻችን ነው።

በፍቅር ካልተነሳን ሩቅ የሚወስድ ሌላ መነሻ አይኖረንም። ውብ ፍጻሜዎች በፍቅር የሚጀምሩ ናቸው። መነሻችንን ፍቅር ካደረግን ከህልማችን ወደብ የማንደርስበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ኢትዮጵያ ንጹህ ናት። ያጠየማት ፖለቲካው ነው። ከፖለቲከኞች ወደሕዝብ የሚነፍሰው የራስወዳድነት ንፋስ ነው ያኮሰሳት።

ወደቀደመ ከፍታችን እንነሳ ዘንድ ከሕዝብ ወደፖለቲከኞች የሚነፍስ ንፋስ ያስፈልገናል። ያልጸዳ ፖለቲካ የጸዳች ሀገር አይፈጥርም። ዛሬ ላይ በሁሉ ነገራችን ቆሽሽን በዘረኝነት ዜማ የቆምነው ባልጸዳ ፖለቲካ ነው።

ፍቅር ዘር የለውም። ፍቅር እኔን ብቻ ይድላኝ አይልም። ፍቅር በደልን አይቆጥርም። ለዛም ነው ፍቅር ከሆነው ሕዝብ የሚነፍስ የፍቅር ንፋስ ያስፈልገናል የምለው። ብዙ ተጉዘን ከኢትዮጵያዊነት ወደ ብሄርተኝነት፣ ከእኛነት ወደእኔነት መጥተናል። ከአንድነት ወደመለያየት፣ ከፍቅር ወደጥላቻ ዝቅ ብለናል። ፍቅር የሌለው እውቀት ወደሞት ካልሆነ ወዴትም የሚወስድ ስፍራ የለውም።

ፍቅር ብቻውን ሥርዓት ነው። ፍቅር ብቻውን ሕገመንግሥት ነው። ፍቅር ካለ ይቅር ለመባባል እና ተነጋግሮ ለመግባባት መንገድ አናጣም። የተግባቦት መንገዶቻችን የተዘጉት ፍቅር ስላጣን ነው። እናም ወደእርቅና ወደቀደመው ፍቅራችን በሚወስደን ብሄራዊ ምክክር ላይ ያጣናት ኢትዮጵያ ትመለሳለች ብለን እናምናለን።

ብሄራዊ ምክክር ብዙ ስም ቢኖረውም አንዱና ዋነኛው መገለጫው ግን የይቅርታ መድረክ የሚለው ነው። ፍቅር የሚመለሰው፣ አብሮነት የሚመጣው እንዲህ ባለው መነጋገርን ባስቀደመ ትውውቅ ነው። ይቅርታ ፍቅርን የሚያውቁ ሁሉ የሚናገሩት የነፍሶች ቋንቋ ነው። የይቅርታ ልብ ሁሌ ያማረ፣ ሁሌ የፈካ የፀሀይ መውጫ አናት ነው...በብርሃን የተሞላ። ይቅርታ ሳንሞት ህያው ሆነን በትውልድ ልብ ውስጥ የምንኖርበት ጥበባችን ነው።

ይቅርታ ክፉዎችን ማሸነፊያ፣ እብሪተኞችን መርቻ በትረ ሙሴአችን ነው። በዓለም ላይ በበጎ ሥራቸው በትውልድ ልብ ውስጥ ደምቀው የተጻፉ ነፍሶች ይቅርታ አድራጊዎች ነበሩ። በአሁኑ ሰዓትም በዓለም ላይ ደስተኛና ስኬታማ ሆነው የምናያቸው ሰዎች ከሁሉ ነገራቸው በላይ ፍቅርና ይቅርታን ያስቀደሙ ናቸው። ፖለቲካችን ከፍቅር ከጥሎ ይቅርታ የዋጀው የሥርዓት አውድ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ላይ ዋጋ እያስከፈሉን ያሉ ነገሮች ሁሉ ባልተፈጠሩ ነበር።

እግዚአብሄርን የሚፈራ ልብ ሁል ጊዜ ይቅርታ ያደርጋል። የፈረሱ ትዳሮች፣ የፈረሱ ጓደኝነቶች፣ ጸጸት የዋጣቸው ትናንቶች ባጠቃላይ ያልተሳኩ ሰዋዊ ትልሞች ሁሉ ይቅርታ የሌለባቸው ናቸው። እንደሀገር ወደህልማችን እንድንጠጋ፣ ወደአንድነት እና ወደ መግባባት እንድንሸጋገር ይቅር የሚል ልብ ያሻናል።

አንዳንድ ነገሮች ቀላል ናቸው.. እውቀት እና ጥበብ ሳይጠይቁ በፍቅርና በይቅርታ ብቻ የሚረቱ ሆነው እናገኛቸዋለን። ህልም በይቅርታ እንደሚፈጠር ፤ ጥላቻ በፍቅር እንደሚሞት ስንቶቻችን ተረድናል? ምንም ይሁኑ የኢትዮጵያ ችግሮች በፍቅር የሚፈርሱ ናቸው። ምንም ይሁን ፖለቲካችን በይቅርታና እውቀት ባለበት ፍቅር የሚነጻ ነው።

ብዙ የሥነአእምሮ እና የሥነልቦና ጠበብቶች ፍቅርን የምንም ነገር መነሻ ያደርጉታል። ሕይወት ከልብ እና ከአእምሮ ነው የሚጀምረው። ልብና አእምሯችን ውስጥ ባለው ሃሳብ፣ ባለው ሥብዕና፣ ባለው ማንነት፣ ባለው አረዳድ፣ ባለው እውቀት እና ማስተዋል ሕይወት ይወለዳል። ፖለቲካ ልብና አእምሯችን ውስጥ ያለው የሃሳብ እና የአረዳድ ነጸብራቅ ነው ። ፖለቲካችን እንዲጸዳ አእምሯችን ከዘረኝነት እና ከራስወዳድነት ሊጸዳ ያስፈልጋል።

የአንድ ሰው የእውቀቱ ጥግ፣ የሥልጣኔው አጽናፍ የሚለካው በልቡ ውስጥ ባለው የፍቅርና የመልካምነት ብዛት ነው። ዓለም በሚሳሳቱና ልክ ባልሆኑ ሰዎች እንደተሞላች መረዳት ፍቅር እና ይቅርታን እንድናውቅ እድል ይሰጠናል። መልካምን የማታውቅ ነፍስ ከአምላክ ዘንድ አይደለችም። ‹በእግዚአብሄር መንፈስ የሚመላለሱ እነሱ የእግዚአብሄር ልጆች ናቸው› የሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ አውቃለው። የእግዚአብሄር መንፈስ ምንድነው? ምን አይነት ነው? ብለን ብንጠይቅ የፍቅርና የይቅርታ መንፈስ እንደሆነ እንደርስበታለን። የእግዚአብሄር መንፈስ ከፍቅር ጀምሮ በፍቅር የሚያበቃ ነው።

እዚህ ምድር ላይ በመልካም ሥራችን ለሌሎች ክብርና ሞገስ ከመሆን ውጪ መጠሪያ ስም የለንም። በምድር ቆይታችን በሥራችን ከመደሰትና ሌሎችን ከማስደሰት ባለፈ ታላቅ ጀብድ የለንም። ሥራችን ነው የሚቀረው። ስማችን፣.. ተግባራችን ነው በትውልድ ልብ ውስጥ የሚቀረው። እናም በእውነት እና በታማኝነት በፍቅርም ኢትዮጵያን ማገልገል ስንኖር መከበሪያችን ስንሞት ደግሞ መጠሪያችን ይሆናል።

ሁሉም ነገር በጊዜ የተገደበ ነው። ይሄ ዓለም ትናንት የሌሎች ነበር ዛሬ ደግሞ የእኛ ሆኗል። ነገ የሌሎች ከመሆኑ በፊት በጊዜአችን ላይ ስማችንን የሚያስጠራ፣ ታሪካችንን የሚመልስ የፍቅር ሥርዓት እንገንባ። ኖረን ለመሞት ሳይሆን ሞተን ለመኖር የሚያበቃ በጎ ሥራን እንትከል። በትውልድ ውስጥ ዳግም መፈጠር ለጥቂቶች የተቻለ ለብዙሃኑ ግን ምኞት የሆነ ነገር ነው። በሌሎች መልካምነት እንደተፈጠርን ሁሉ በእኛ መልካምነትም የሚፈጠሩ ስላሉ ልቦቻችንን ለበጎ ሥራ እናሰናዳ።

# የሰብል ጥበቃውን በጋራ ርብርብ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**



መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ 2011 ዓ.ም ለኢትዮጵያ፣ ሶማሊያና ኬንያ እንዲሁም አጎራባቻቸው እጅግ ፈታኝ ጊዜ ነበር። ያ ዓመት የበረሃ አንበጣ መንጋ በሀገሮቹ በከፍተኛ ሁኔታ ጉዳት ያደረሰበት ነበር። ከኬንያ ውጭ ባሉ ሀገራት መሰል የአንበጣ መንጋ ሲከሰት ከ25 ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ያ ወቅት በተለይ በኬንያ ከ70 ዓመታት በኋላ አስከፊ የአንበጣ መንጋ የተከሰተበት ወቅት ሆኖ ተመዝግቧል። የአንበጣ መንጋ ወረርሽኙ ግዙፍ ሲሆን፤ የአፍሪካ ቀንድንና ደቡብ እስያን እያካለለ ያገኘውን ሰብል በማውደም የአካባቢውን ሕዝብ የምግብ አቅርቦትና ሕይወት አደጋ ላይ ጥሏል።

በወቅቱ መንጋውን ለመከላከል መንግሥት ብቻ ሳይሆን ዓለምአቀፍ ተቋማትም ርብርብ አድርገዋል። አርሶ አደሩም ሴት፣ ወንድ፣ ሕፃን ሽማግሌ ሳይል ድምፅ እያወጣ፣ ጢስ እያጤሰ መንጋውን ለመከላከል ርብርብ አድርጓል። ሥራው ግን ከባድ እንደነበር መረጃዎች ያስታውሳሉ። አብዛኛው ጉዳት የደረሰው በደን ላይ ቢሆንም በአዝእርት ላይም እንዲሁ ጉዳት ደርሷል፤ የአርሶ አደሮች ሰብል ወድሟል። የተለያዩ የዜና አውታሮች እንደዘገቡት ደግሞ 2014 ዓ.ም በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት የአንበጣ መንጋ አስጊነቱ ቀንሷል።

የምሥራቅ አፍሪካ የበረሃ አንበጣ መከላከል ድርጅቱ ያወጣው መረጃ እንደሚያሳየው፤ በተጠቀሰው ዓመት ኢትዮጵያና ኬንያን ጨምሮ በቀጣናው ሀገራት ዝቅተኛ ዝናብ መኖሩ እንዲሁም በአካባቢው የተከሰተው ድርቅ የአንበጣ መንጋውን እንዳይፈለፈል አድርጎታል። አንበጣ ዋና መፈልፈያው እርጥበት ማግኘት ስለሆነም በቂ እርጥበት አለመኖሩ፣ አንበጣው እንዲዳከምና የመቀነስ አዝማሚያ እንዲያሳይ አድርጎታል።

መረጃው እንዳመለከተው፤ የአንበጣ መንጋው ከፍተኛ መጠን ያለው ነው። ቁጥሩም እስከ 10 ቢሊዮን ሊሆን ይችላል። የሚሸፍነውም ቦታ በመቶዎች ኪሎ ሜትር ሲሆን፤ በቀን እስከ 200 ኪሎ ሜትር በመሸፈን ያገኘውን እየበላ በመራባት የአርሶ አደሮችን ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥል ነው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የምግብና የእርሻ ድርጅት እንደገለፀውም የአንበጣ መንጋው በአማካይ 2500 ሰዎችን ለአንድ ዓመት የሚመግብ ምርትን ሊያወድም ይችላል። እናም ከጅምሩ እርሱን መከላከል የውዴታ ግዴታ ሆኖ ካልቀጠለ አደጋው ይከፋል። ስለዚህም ሁሉም በተቻለው መጠን ሳይከሰት ለመከላከል፤ ከተከሰተ ደግሞ በተለያዩ አማራጮች መፍትሄ ለማፈላለግ መስራት ይኖርበታል።

የአንበጣ መንጋውን በቋሚነት ለመከላከል ሥራዎች ቢከወኑም እርሱን በቋሚነት ማጥፋት ያዳግታል። በመሆኑም ትንበያዎችን እየተከታተሉ ቅድመ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ማሳያው ከሰሞኑ አንበጣው በስፋት የታየባቸው ክልሎች ሲሆኑ፤ እንደየክልሉ ሁኔታና የአንበጣ መከሰት አቅም ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን የክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊዎች ይገልጻሉ። አንበጣው በድጋሚ እየተራባ እንደመጣና ለመከላከል ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን የትግራይ፣ አማራና አፋር ክልሎች እየገለጹ ይገኛሉ። ግብርና ሚኒስቴርም እያገዛቸው መሆኑን ያስረዳሉ።

የምሥራቅ አፍሪካ የበረሃ አንበጣ መከላከል ድርጅት በበኩሉ የአንበጣ መንጋውን አስቀድሞ ለመከላከል እና ከተከሰተም በቶሎ ለመቆጣጠር እንዲያስችል የመሠረተ ልማቶች ግንባታ እየተከናወነ መሆኑን ያመለክታል፤ በኢትዮጵያም በተለያዩ አካባቢዎች ላይ ተዛማጅ ተባዮችን የመከላከያ ማዕከላት እየተቋቋሙ እንደሆነም ይገልጻል። ይህ ሁሉ ተግባር ምን መልክ ይዟል፤ ክልሎች የት ላይ ናቸው፤ ግብርና ሚኒስቴርስ ምን ያህል ዝግጁነት አለው የሚሉና መሰል ጥያቄዎችን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለሚመለከታቸው አካላት አንስቷል።

በአፋር ክልል ከሰብል ጥበቃ ጋር በተያያዘ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን የክልሉ የእንስሳት፣ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታውቋል። የቢሮው የዕጽዋት ጥበቃ ዳይሬክተር አቶ ሀቢብ አብደላ እንዳሉት፤ የሰብል ጥበቃ ሥራው በተለያየ መልኩ እየተከናወነ ይገኛል። አንዱ በክልሉ የተከሰተውን የአንበጣ መንጋ የመከላከል ተግባር ሲሆን፤ ክልሉ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመሆን የተለያዩ ሥራዎች እያከናወነ ነው።

መንጋው በአረንጓዴ ዐሻራ በተተከሉ ችግኞችና ለእንስሳት ምግብ በሚሆኑ ተክሎች ላይ ጉዳት እያደረሰ መሆኑን ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፣ መነሻው ደግሞ ከቀይ ባህር አካባቢ መሆኑን ይናገራሉ፤ የአንበጣ መንጋው መታየት የጀመረው ከሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ነው። የመከላከል ሥራው ወዲያው የተጀመረ ባለመሆኑም ከአፋር ክልል አልፎ የትግራይ አጎራባች ዞኖች ላይም እንዲከሰት አስችሎታል ሲሉ አቶ ሀቢብ ይጠቁማሉ።

የአንበጣ መንጋው በክልሉ በሚገኙ 15 ወረዳዎች ላይ ጉዳት እያደረሰ የሚገኝ እንደሆነ ያነሱት አቶ ሀቢብ፤ አንበጣው በተለይ ግመሎችና ፍየሎች የሚመገቧቸው ተክሎች ላይ እንዲሁም በቅርቡ በአረንጓዴ አሻራ መርሃግብሮች የተተከሉ ችግኞች ላይ ጉዳት እያደረሰ ነው ብለዋል። መንጋው የተከሰተበት ወቅት የደረሱ ሰብሎች በሚሰበሰቡበትና የእርሻ ስራ በሚከናወንበት ወቅት በመሆኑ በከፊል አርብቶ አደር አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች ላይ ጉዳት ያስከትላል የሚል ስጋት እንዳለም ነው የገለጹት።

የአንበጣ መንጋው እስካሁን በተክሎች ላይ ያደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ክልሉ መረጃ በማሰባሰብ ላይ እንደሚገኝ የሚናገሩት ዳይሬክተሩ፤ ክልሉ ከመረጃ ማሰባሰብ ጎን ለጎን የመከላከል ሥራውን ማጠናከር ላይ እየሠራ ነው። የክልሉ መንግሥት ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበርም ከሐምሌ 18 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ መንጋውን የመከላከል ሥራ እያከናወነ ነው ሲሉ ያብራራሉ።

በዚህ ደግሞ ከትግራይ ክልል ተነስቶ ወደአፋር ክልል በመጓዝ ጉዳት ሲያደርስ የነበረውን የአንበጣ መንጋ ከመነሻው መቆጣጠር መቻሉን ጠቅሰው፤ ግብርና ሚኒስቴር የባለሙያ፣ የበጀትና የኬሚካል እንዲሁም ሌሎች ድጋፎችን ያደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል፤ ችግሩን ለመቆጣጠር የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም ያስገነዝባሉ። የአንበጣ መንጋውን ሙሉ በሙሉ ማጥፋት እስከሚቻልበት ጊዜ ድረስ ከትግራይ ክልልና ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በጋራ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ የመፍጠርና መንጋውን ለመከላከል የሚረዱ የግብዓትና የበጀት ድጋፎችን ከአጋር ድርጅቶች ማሰባሰብም ይገባል። ለዚህ ደግሞ ክልሉ ቁርጠኛ ሆኖ ይሠራል፤ አሁን ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አንበጣ የት፣ እንዴትና መቼ እንደሚራባ ለባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠት አስፈላጊውን የመከላከል ሥራ ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ነው።

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮም እንደ አፋር ሁሉ ክልሉ ተለይቶ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የምርት ዘመኑን ግብና ዕቅድ አዘጋጅቶ በርካታ ሥራዎችን እንዳከናወነ የቢሮ ኃላፊ ዶክተር ኃይለማርያም ከፍያለው ይናገራሉ። በተለይም ከሰብል ጥበቃ አንጻር የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

**ችግሩን ለመከላከል ስድስት አውሮፕላኖች ተዘጋጅተዋል፤ የተሰራጨውን ኬሚካል የሚረጩ ስምንት መኪናዎች ከ11 ባለሙያዎች ጋር ወደ አካባቢዎቹ ተልከዋል**

‹‹እንደ ክልል አሁን ያለንበት የክረምት ወቅት ዝናብ ወጣ ገባ የሆነበት ነው። ይህ ደግሞ ለተባይ መፈጠር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። እናም እንደ ክልል የሰብል ጥበቃን በተመለከተ ብዙ ሥራዎች ማከናወን እንዳለብን ተገንዝበናል›› ያሉት ዶክተር ኃይለማርያም፤ በምስራቅ አማራ በኩል ያሉ አካባቢዎች ለዚህ ተጋላጭ ሆነዋል። የተምች ወረርሽኙና የአንበጣ ወረርሽኝ በተከታታይ አጋጥሟቸዋል። የፌዴራል መንግሥት የኬሚካል አቅርቦቱን ትኩረት አድርጎ ሲከታተለው ስለነበር እንደ ወረዳና ክልል ከፍተኛ ርብርብ ተደርጎ የተምች ወረርሽኙን ጉዳት ሳያደርስ መከላከል ተችሏል ይላሉ።

በአካባቢው የተከሰተውን የአንበጣ ወረርሽኝ ግን ገና ለመቆጣጠር እየተሠራ እንደሆነ የጠቀሱት ኃላፊው፤ አሁን ባለው ሁኔታ ወረርሽኙ ሦስተኛ ዙር ጭምር ሊከሰት እንደሚችል ስጋት መኖሩንም አመልክተዋል። ስለሆነም ትኩረት ሰጥተን በእኛ በኩል ለመስራት እንሞክራለን። ሕዝቡና የሚመለከታቸው አካላትም በዚህ ጉዳይ ላይ ርብርብ ሊያደርጉ ይገባል ይላሉ።

የትግራይ ክልል የእርሻ ተፈጥሮ ሀብትና የአፈር ልማት ማሻሻል ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ገብረስላሴ ከአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ ጋር የሚስማማ ሃሳብ አላቸው። ሃላፊው መንጋው እንዲጠፋና ጉዳት እንዳያደርስ ማድረግ የሚቻለው ተቀናጅቶ መሥራት ሲቻል እንደሆነም ያምናሉ። የበርሃ አንበጣ መንጋው የክልሎችን ድንበር የሚሻገር መሆኑን ጠቅሰው፣ በመከላከሉ ላይ የፌዴራል መንግሥት ሥራ እንዳለ ሆኖ ክልሎችም ተጋግዘው መሥራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የትግራይ ክልል በዚህ የመኸር ወቅት ችግር ሊሆን ይችላል ተብሎ ከሚያስበው ውስጥ አንዱና ዋነኛው የሰብል ጥበቃ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም በክልሉ የአንበጣ መንጋ በምስራቃዊና ደቡብ ምስራቅ አካባቢ እየታየ ነው። አስቀድሞ በነበረ ትንበያ መሠረት ግን ከወዲሁ ግብረ ኃይል በማዘጋጀት አሁን ላይ በፍጥነት ወደ መከላከል ሥራ ተገብቷል። ሥራው የአንድ ወቅት ብቻ አይደለምና ዝግጁ ሆኖ መጠበቅ እንዲሁም ሁሉም አመራርና ህዝብ በትኩረት መሥራት ይኖርበታል ሲሉ አስገንዝበዋል።

የግብርና ሚኒስቴር የዕፅዋት ጥበቃ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ በላይነህ ንጉሤ እንዳሉት፤ በክልሎች የተከሰተው የአንበጣ ወረርሽኝ ብዙ አደጋ እንዳያደርስ ቀደም ብሎ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። ከተከሰተም በኋላም ቢሆን ለመከላከል የሚያስችሉ ዝግጅቶች ተደርገዋል። ለአብነት በክልሎች ላይ ለተከሰተው የአንበጣ ወረርሽኝ መከላከል የሚውል 41 ሺህ 500 ሊትር የተለያዩ የኬሚካል አይነቶች ተሰራጭተዋል።

አቶ በላይነህ እንዳመለከቱት፤ ችግሩን ለመከላከል ስድስት አውሮፕላኖች ተዘጋጅተዋል፤ የተሰራጨውን ኬሚካል የሚረጩ ስምንት መኪናዎች ከ11 ባለሙያዎች ጋር ወደ አካባቢዎቹ ተልከዋል።

መሪ ሥራ አስፈጻሚው አሁን የተከሰተው ወረርሽኝ የከፋ አይደለም ሲሉ ጠቅሰው፣ ይሁንና እያደር የመበራከታቸው ነገር ሊመጣ ይችላልና ሁለቱ አውሮፕላኖች የኬሚካል ርጭት ሥራ እንዲጀምሩ ሆነዋል ብለዋል። የአንበጣ መንጋ ወረርሽኝ በክልሎች ተከስቶ በሰብል ላይ ጉዳት ከማድረሱ በፊት ለመከላከል የተለያዩ ኬሚካሎች ክልሎች ተደራሽ መደረጋቸውን ጠቅሰዋል፤ ለኦሮሚያ ክልል 12 ሺህ፣ ለአማራ 10 ሺህ 500፣ ለትግራይ ሰባት ሺህ ፣ለአፋር አንድ ሺህ፣ ለደቡብ ሦስት ሺህ፣ ለደቡብ ምዕራብ ሁለት ሺህ ሊትርና ለሌሎች ክልሎችም ተደራሽ የማድረግ ሥራ እንደተሠራም ያነሳሉ።

በክልሎች የተከሰተው የአንበጣ መንጋ ወረርሽኝ በሰብል ላይ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ በሚደረገው የመከላከል ሥራ በቂ የኬሚካል ክምችት ባይኖርም ያለውን ችግር ሊቋቋም የሚችል የኬሚካል ክምችት አለ ሲሉ ጠቅሰው፣ የመከላከል ትግበራውም በትኩረት እየተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የአንበጣው ወርርሽኝ የማጥቃት ደረጃው እየተጠና ኬሚካል መርጨት፤ የሚያስፈልገውን የመለየት ሥራ እየተሠራ ነው። በትግራይ ክልል በባህላዊ መንገድ የመከላል ሥራ እየተሠራ ሲሆን፣ የተላኩት ባለሙያዎችና መኪናዎች በክልሉ ካሉት የግብርና ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት እየሠሩ ይገኛሉ።

በክልሎች የተከሰተው ወረርሽኝ እያደረሰ ያለው ጉዳት የከፋ ባለመሆኑ ተራራማ ቦታዎችን ኬሚካል ለመርጨት አንድ አውሮፕላን በቂ ነው ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፣ አንድ አውሮፕላን ሁለት ሺህ ሊትር ኬሚካል የመርጨት አቅም አለው። አንድ ሊትር ኬሚካል ደግሞ አንድ ሄክታር መሬት መሸፈን ይችላል ብለዋል። ተቋሙ የአንበጣ ወረርሽኝና ፀረ ሰብል ተባዮችን ለመከላከል በቀጣዮቹ ጊዜያትም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሠራበት እንደሚሆን አስታውቀዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የትምህርት ጥራት ችግር መፍትሔው እንዳይርቅ

ገርማ መንግሥቴ



በሀገራችን የትምህርት ጥራት ጉዳይ ዘመን አመጣሽ አገላለፅ፣ ወይም ጽንሰ-ሃሳብ ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በቀድሞው ጊዜ የትምህርት ጥራት ጉዳይ ብዙም አሳሳቢ ሆኖ ይገኝ ስላልነበረ ነው። “አሳሳቢ ሆኖ ይገኝ ስላልነበረ” ሲባል ግን የትምህርት ጥራትን አስመልክቶ ግንዛቤው ስላልነበረ፤ ወይም፣ የትምህርት ጥራት አስፈላጊ ስላልነበረ ማለት አይደለም። ሁሌም ቢሆን የትምህርት ጥራት እጅግ አስፈላጊ ነው። ልዩነቱ ግን በቀደመው ዘመን በትምህርት ጥራት ጉዳይ የሚደራደር አካል አልነበረም። ከተማሪው እስከ አስተማሪው ሁሉም እውቀትን ፍለጋ ይኳትንም ነበር።

ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ኩረጃ ከውርደትም በላይ ሞት ነው። ምንም እንኳን የቤት ሥራ አለመሥራት የሚያስቀጣ ቢሆንም ሰነፍ መባል እራሱ ከቅጣት በላይ ነው። ከፍተኛ የሥነልቦና ጉዳትም በሰነፍ ተማሪ ላይ ያሳድራል። በፈተና መውደቅ እስከ ቤተሰብ ድረስ የዘለቀ ኀዘንን ያስከትላል። “የእከሌ ልጅ ወደቀ፤ የእከሌስ? እሱማ አለፈ እኮ - - -” መባል በራሱ እስከ ጎረቤት ድረስ ለቁጭት ያበቃል፤ ለኀዘንም ይዳርጋል።

በዩኒቨርሲቲዎችም ኩረጃ የባሰ ውርደት ሲሆን፣ መመረቂያን በገንዘብ ለማሰራት ቀርቶ አንዲት የሌላ ሰው ቃል እንኳ ያለ አግባብ ወደ ጥናቱ ውስጥ ጥልቅ እንዳትል ይደረግ የነበረው ጥንቃቄ ደም የመስጠት ያህል ነበር። ያን ጊዜ በትምህርት ቀልድ አልነበረም። ከዚህ አንፃር የትምህርት ጥራት ጉዳይ ብዙም አጀንዳ አልነበረም። በአሁኗ ኢትዮጵያስ?

በአሁኑ ጊዜ የትምህርት ጥራት ጉዳይ ተረት እየሆነ የመጣ ይመስላል። በሁሉም የትምህርት እርከኖች በሚባል ኩረጃና በትምህርት መውደቅ ባህል እየሆኑ መጥተዋል። የአሠራር ሥርዓት ሁሉ መስለው ፤ በማስታወቂያ ተደግፈው ለአደባባይ ሲበቁ እየታዩ ነው። ለምሳሌ በዩኒቨርሲቲዎች በር ላይ መመረቂያ ጽሑፍን በተመለከተ “እናማክራለን”፣ “ፕሮፖዛል እናዘጋጃለን”፣ “ስክሪፕት እንፅፋለን”፣ “የአርትኦት ሥራ እንሰራለን ... ወዘተ” የሚሉ ማስታወቂያዎችን በገፍ ማየትና ማንበብ የተለመደ ሆኗል። ኮምፒውተር ይዘው ቁጭ ያሉ ጸሐፊዎች “መመረቂያ ጽሑፍ እዚህ አለ” የሚል በትልቁ ጽፈው መመልከትም ብርቅ አይደለም። ጊዜ ያለፈበትን መመረቂያ ጽሁፍ ወቅታዊ አድርገው ጠርዘውና በቀለም ሳይቀር ኩለውና ኳኩለው በ5 ሺ ብር መቸብቸብ ተለምዷል።

በአሁኑ ጊዜ ከትምህርት ፍትሃዊነት፣ ተደራሽነትና ጥራት ጋር በተያያዘ ያለው ችግር በራሱ ትምህርትን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳ ነው የሚመስለው። ከታች እስከ ላይ ችግር አለ። ከጥግ እስከ ጥግ ተተረማምሷል። ችግሩ በተማሪ ሳይወሰን አስተማሪውንም እየሰለቀጠው ነው። ኩረጃ ከታችም አልፎ ላይ ድረስ ዘልቋል። ምንተፋ (plagiarism) የትጉሃን ተግባር እየሆነ ነው። የሀሰት የትምህርት ማስረጃን መሸመት የተማሪው ብቻ መሆኑ ቀርቶ የአስተማሪውም ተግባር ሆኗል።

የትምህርት ጥራት ችግር ለማሸቀልቀሉ አጃቢዎች ተማሪውና አስተማሪው ብቻ አይደሉም። የሲቪክ ተቋማት ሳይቀሩ ባለ ሀሰት ዲግሪዎች መናኸሪያዎች ከሆኑ ሰነበቱ። ማጭበርበራቸው የተነቃባቸው ከሥራቸው ዝቅ ቢደረጉም ያልተደረሰባቸው ጭራሽ ወደ ላይ ሲወጡ ለማየትም ሆነ በትርኢቱ ዘና፣ ፈታ ለማለት ሲኒማ ኢትዮጵያ ወይንም ብሄራዊ ትያትር መሄድ አያስፈልግም። ከላይ የተጠቀሱት የሞራል ጥሰቶችና የሥነ ምግባር ግድፈቶች እንዳሉ ሆነው ለትምህርት ጥራት ችግር መንስኤዎቹ ምንድን ናቸው? የሚለውን መመልከቱ ገቢ ነው።

ከባለሙያዎች፣ ጥናትና ምርምሮች፣ እንዲሁም ከራሳችን የመማር-ማስተማር ተሞክሮ እንደምንረዳው፣ የትምህርት ግብዓቶች አቅርቦት እጥረት ወይም ጭራሽ አለመኖር፤ የመማር-ማስተማር ከባቢ ሁኔታ አለመመቸት፤ የክፍል ውስጥ የተማሪዎች አያያዝ፤ የማስተማር ሥነ ዘዴ፣ የትምህርት መሣሪያ እጥረት ወይም ጭራሽ አለመኖር ፣ የተጓዳኝ ክበባት አለመኖርና የተማሪዎች ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን ፣ በእቅድ የአለመመራት ሁኔታ፣ የትምህርት አመራር፣ አሠራርና አደረጃጀት ማሻሻያ መርሃ-ግብር ተግባራዊ አለመደረግና የመሳሰሉት ለትምህርት ጥራት መጓደል የየራሳቸው አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ያለ መማሪያ-ማስተማሪያ መጻሕፍት የትምህርት ጉዳይ ባዶ ነው። የመምህሩም ሆነ ተማሪዎች ልፋት ከንቱ ነው። ፖሊሲም ሆነ ሥርዓተ ትምህርት ዋጋ የላቸውም። የተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ አይታሰብም። የትምህርት ተደራሽነት ብሎ ነገር ጉንጭ አልፋ ይሆናል። የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ሹፈት ካልሆነ በስተቀር እውን ማድረግ አይቻልም። የተማረ የሰው ኃይል ማፍራት ብሎ ነገር ከሃሳብ ያለፈ ገቢር የለውም።

ይህ ማለት የመማሪያ-ማስተማሪያ መጻሕፍት እጥረት ካለ የትምህርት ጥራት ችግር አለ ማለት ነውና ችግሩን ለመቅረፍ ከመማሪያ-ማስተማሪያ መጻሕፍት ፍላጎትና አቅርቦት መጣጣም አኳያ መሥራት ይጠበቃል ማለት ነው። ይህም ከትምህርት ጥራት ችግር መንስኤዎች አንዱ ሆኖ ይወሰዳል።

በኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት ችግር ስለ መኖሩ አንዱ ማረጋገጫ በ2014 ዓ.ም በአገር አቀፉ ፈተና ላይ በተደጋጋሚ ሲያጋጥሙ የነበሩ ኩረጃዎችንና የፈተና ስርቆቶች ለመከላከል የተወሰደው ርምጃ ነው። ያለፈው ዓመት ተፈታኞች በተለየ ሁኔታ፣ ማለትም በሀገሪቱ ውስጥ ወዳሉ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ገብተው በጥብቅ ቁጥጥር ስር እንዲፈተኑ ተደርገዋል። የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተፈታኞች ዝቅተኛ ውጤት አምጥተዋል። ከ96 በመቶ በላይ የሆኑትም እንዳልተሳካላቸውም ተገልፆ ነበር።

አስደንጋጭ የተባለው ውጤት እንደሚያሳየው ለፈተና ከተቀመጡት ከ980 ሺህ በላይ ተማሪዎች መካከል 30 ሺህ ገደማዎቹ ብቻ ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ያገኙ መሆናቸው ነው። የ2014 የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል አብዛኞቹ ዝቅተኛ ውጤት ያመጡበት ምክንያት ምን ይሆን?” ተብሎ በመላው ሀገሪቱ ለተነሳው ጥያቄ አንዱና ዋነኛው መልስ የትምህርት ጥራት ችግር ነው። በተለያዩ ጉባዔዎች ለምሳሌ በ31ኛው ሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባዔ ፊት መሪው አጀንዳ የነበረውም ይሄው የትምህርት ጥራት ጉዳይ ነው።

በዚሁ ዓመት የዓለም ባንክ ባወጣው መረጃ መሠረት ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሰሃራ በታች የአፍሪካ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ሊያጠናቅቁ የተቃረቡ ሕፃናት ማንበብ አይችሉም። ኢትዮጵያ ውስጥ ከ85 በመቶ በላይ ዕድሜያቸው 10 የደረሰ ሕፃናት ቀለል ያለ ጽሑፍ እንኳን አንብበው መረዳት አይችሉም። ይህም መረጃ የኢትዮጵያ የትምህርት ደረጃ ወዴት እየሄደ እንደሆነ ያመላክታል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ጥናት እና ምርምር ተቋም ዳይሬክተር የሆኑትና በኢትዮጵያ የትምህርት ሁኔታ ላይ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባበር በርካታ ጥናቶችን ያካሄዱት በላይ ሃጎስ (ዶ/ር) የጥናት ግኝታቸውን አስመልክተው እንደተናገሩት፣ በፈረንጆቹ 2021 በተደረገ ጥናት 68 በመቶ የሚሆኑ የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ‘ዜሮ ሪደርስ’ [ምንም ማንበብ የማይችሉ] ናቸው። 51 በመቶ የሚሆኑ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ አንብበው መረዳት አይችሉም።

ተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል የሚዘዋወሩት ብቃታቸው ተፈትሾ አይደለም። ዘንድሮ በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ለመጣው ውጤት ተጠያቂው የሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ነው። ይህ ውጤት “የትምህርት ሥርዓቱ የወለደው” ነው። የትምህርት ሥርዓቱ ልጆች ብቃት እንደሌላቸው እየታወቀ ከክፍል ወደ ክፍል እንዲዛወሩ ይፈቅዳል። በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት ከ8ኛ እና 10ኛ ክፍል በቀር ሁሉም ተማሪዎች ወደሚቀጥለው ክፍል እንዲሸጋገሩ መደረጉ ለትምህርት ጥራት መውደቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

ከዚህ አኳያ የትምህርት ሥርዓቱ ካልተስተካከለ በቀር ለውጥ ሊመጣ አይችልም። መምህራን የዚህ አይነት ውጤት ባለቤት እንዲሆኑ ያደረጋቸውም የትምህርት ሥርዓቱ ነው። የተማሪዎቹ ውጤት ለኢትዮጵያ “እንደ ማንቂያ ደወል” ነው። የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች የውጤት ማሽቆልቆል “ለዓመታት ሲንከባለል የቆየ የበርካታ ችግሮች መገለጫ እና ተሸፍኖ የቆየውን እውነተኛ የትምህርት ሥርዓት ያለበትን ደረጃ ያመለከተ ነው።” ሲሉም የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ተናግረዋል።

ምንም እንኳ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናት የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ቢደረገም፣ በኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት ጉዳይ ዛሬም ድረስ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ይገኛል ሲል (ራይዝ ኢትዮጵያ፣ እ.ኤ.አ 2021) ገልጿል። ኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት ደረጃዋን ከፍ ለማድረግ የጀመረችውን ጥረት አጠናክራ መሥራት አለባት። አዳጊ በሚባሉ ክልሎች እና ገጠራማ ሥፍራዎች ያሉ ሕፃናት ጥራት ያለው ትምህርት እያገኙ አይደለም። ይህም በውጤታቸው ላይ እየተንፀባረቀ ይገኛል። ትምህርት ጥራት ይጎድልባቸዋል በሚባሉ አካባቢዎች ያሉት ዐበይት ችግሮች የመማሪያ ቁሳቁስ እጥረት እና የተሟላ ትምህርት ቤት አለመኖር ናቸው ሲል የጣሰው ወደልሃና (ዶ/ር)፣ ፕሮፌሰር ሪካርዶ ሳባቴስ እና ዳዊት ጥበቡ (ዶ/ር) የጋራ ጥናት ጠቁሟል።

የትምህርት ጥራት መጓደል ዘርፉ የሚፈልጋቸውን ባለሙያዎች እንዳያገኝ፤ ጠያቂና ችግር ፈቺ፣ ሃሳብ አፍላቂ ምሁር እንዳይኖር ያደርጋል። የፈጠራ ሰዎች ይጠፋሉ። ከተማረ ሃይል የሚጠበቀው የባህሪ ለውጥ አይመጣም። የትምህርት ተቋማት ከስርቆት የፀዱ እንዲሆኑ የሚደረገው ጥረት እንዳይሳካ ያደርጋል። በራሱ የማይተማመን ትውልድ ይፈጠራል። ከራስ ጥረትና ልፋት ይልቅ በሌሎች ትከሻ ወረቀትን ለማግኘት የሚደረግ ሩጫ ይበራከታል። እውቀትን ከመሸመት ይልቅ ኩረጃን እንደአቋራጭ መንገድ መጠቀም ባህል ይሆናል። ራስ ወዳድነት እየተስፋፋ አገርና ሕዝብን የማገልገል ሃላፊነት ይጓደላል። ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆንና ለዴሞክራሲ ባህል ማበብ አስተዋፅኦ የሚያደርግ ትውልድ አይኖርም። ይህንንም ሁሉም በዚሁ የትምህርት ጥራት መጓደል ላይ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች ይስማሙበታል።

ከለውጡ በፊት በነበረው አስተዳደር፣ በአንድ የወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ዓመታዊ ሪፖርት መግቢያ አንቀፅ ላይ “የትምህርት ዘመኑ ቁልፍ ተግባር የትምህርት ልማት ሠራዊት ለትምህርት ጥራት እውን መሆን ከፍተኛ የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ በመሆኑ በወረዳችን በየደረጃው በሚገኙ አመራሮች፤ ፈፃሚዎች እና ባለድርሻ አካላት በተሻለ ሁኔታ በመደራጀት በላቀ አፈፃፀም እየተከናወነ ይገኛል።” የሚል ሰፍሮ ይገኛል።

በዚህ የክንውን ሪፖርት ላይ ሰፍሮ እንደምናየው ከሆነ “የትምህርት ልማት ሠራዊት” የትምህርት ጥራትን እውን ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል ማለት ሲሆን፤ “በላቀ አፈፃፀም እየተከናወነ ይገኛል” ከሚለውም “የትምህርት ጥራት እየተጠበቀ ይገኛል” የሚል ፌዝ መሳይ ላይ እናገኛለን። ከሆነ እሰየው መሆኑን እየገለፅን ማብራራቱን ለባለሙያዎች ትተን ሌሎቹን እንመልከት።

“የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በተዘረጋው የትምህርት ፍኖተ ካርታ መሠረት ቀደም ሲል በክልሎች ሲከናወኑ የቆዩት የስምንተኛ እና የስድስተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናዎች በፌዴራል ደረጃ እንዲሰጡ” የትምህርት ሚኒስቴር መወሰኑ (በሀዋሳ ከተማ የተካሄደው 31ኛው ሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባዔ ያስታውሷል) ሌላኛው የመፍትሄ አካል ተደርጎ የተወሰደ ስር ነቀል ርምጃ ነው በሚል በብዙዎች ተመስግኗል።

የተሻለ ብቃት ያላቸው ተወዳዳሪ መምህራን ወደ ትምህርት ሥርዓቱ ሊሳቡ ይገባል። ለመምህራን የሚሰጣቸው ዝቅተኛ ክፍያ አንዱ ለትምህራት ጥራት ተጠያቂ ምክንያት ነው። በመሆኑም፣ ማበረታቻ እና ተመጣጣኝ ክፍያ ከግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል። የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በመንግሥት የሚወሰዱ ርምጃዎች ታች ድረስ መውረድ አለባቸው። የችግሩም፣ የመፍትሔውም ወሳኝ አካል መንግሥት ነው።

መንግሥት ንቅናቄውን ከላይ ቢያስጀምረው በተዋረድ እስከ ቤተሰብ ድረስ ይሄዳል። ሁሉም ወገን ሊሳተፍበት ይገባል። ካልሆነ ግን የአንድ ሰሞን ወሬ ብቻ እንዳይሆን ስጋት አለኝ።” የሚለው የዶ/ር በላይ ሃጎስ፤ “ሀገር ለማዳን በሚከፍለው መስዋዕትነት ልክ ትምህርቱን ከወደቀበት ማንሳት የዚህ ትውልድ ሃላፊነት ሊሆን ይገባል ሲል ያስቀምጣል። በእኛ በኩል የለውጥ ሥራዎችን ጀምረናል” የሚሉት ደግሞ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ናቸው።

‹‹የትምህርት ጥራትን የማስጠበቁ ሥራ የተቀናጀ ተግባርን ይጠይቃል። ለዚህም ነው የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ እየተደረገ የሚገኘው። በሙከራ ደረጃ የተጀመረው ከ 1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ዘንድሮ ወደ ሙሉ ትግበራ ተገብቷል። ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያለው ሥርዓተ ትምህርት ደግሞ ዘንድሮ በሙከራ ደረጃ የተጀመረ ሲሆን በቀጣዩ የ2016 ዓ.ም ወደ ሙሉ ትግበራ የሚገባ ይሆናል›› የሚለው የትምህርት ሚኒስቴር የሥራ ሃላፊዎች መግለጫ አንድ ብስራት ይዞ ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹መፍትሔው ጠመንጃ ሳይሆን ዋነኛው አማራጭ ምክክር ብቻ ነው››

-የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ



ምሕረት ሞገስ

ለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አባልነት በማህበረሰቡ በእጩነት ከቀረቡ ከ600 በላይ ሰዎች መካከል ብዙ ሂደቶችን አልፈው 11 ኮሚሽነሮች ከተመረጡ አንድ ዓመት ከአምስት ወራት ተቆጠሩ። ከኮሚሽነሮቹ መካከል በዓዕምሮ ሕክምና ዘርፍ የካበተ ልምድ ያላቸው እና ከ30 በላይ ጥናታዊ ፅሁፎችን ያቀረቡት፤ በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በመዘዋወር ሀገር ያገለገሉት ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ በአስተማሪ እና በመካሪነታቸው ታዋቂነትን ማትረፋቸውን ተከትሎ የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ሆነው መመረጣቸው አይዘነጋም።

በኢትዮጵያ ሀገራዊ መግባባትን የመፍጠሪያ መድረክን ለመምራት የተቋቋመው ይኸው 11 አባላትን የያዘው ኮሚሽን፤ የሠራቸውን ሥራዎች በተለይም ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የተሳታፊ ልየታ ሥራው የደረሰበትን ደረጃ እና ወደ ፊትም በሚሠራቸው ሥራዎች ዙሪያ ከኮሚሽኑ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ ጋር ቆይታ አድርገን፤ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል።

**አዲስ ዘመን፡- ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የተሳታፊ ልየታ ሥራው ምን ላይ ደረሰ?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** እስከ አሁን በአምስት ክልሎች እና በአንድ የከተማ መስተዳድር ላይ ሲሠራ ቆይቷል። በተለይ በሐረር እና በድሬዳዋ በደቡብ ምዕራብ እና በሲዳማ ሰፊ የተሳታፊዎች ልየታ ሥራ ተሠርቶ፤ በአብዛኛው አልቋል። በአዲስ አበባ፤ በጋምቤላ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ደግሞ የተባባሪዎች ሥልጠና ተጠናቆ ወደ ተሳታፊዎች ልየታ እየሔድን ነው።

ከዚህ በኋላ ያለው የሥራ ሒደት ምን ያህል አዋጭ ነው? ምን ምን ተግዳሮቶች አጋጠሙ? በዚህ ፍጥነት ከሔድን ምን ያህል ጊዜ ሊፈጅብን ይችላል? የተባባሪ አካላትን ቁጥር ምን ብናደርገው ይሻላል? በተለይ ባስተዋልነው ሒደት ውስጥ አሁንም የሴቶች ተሳትፎ አመርቂ አይደለም። በተባባሪ አካልነት ወይም ሴቶች በጥሩ ሁኔታ እንዲሳተፉ ለማድረግ መውሰድ ያለብን ርምጃ ምንድን ነው? ብለን ለይተን እንሠራለን።

ተሳታፊዎች በሺ የሚቆጠሩ ሲሆኑ፤ ከየወረዳው ተሰብስበው ከአንድ ዞን 450 ሆነው ሲመጡ፤ የእነርሱን ማቆያ፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ እና የትራንስፖርት ወጪያቸውን እና አጠቃላይ የአበል ክፍያ ራሱ በደንብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። በሌላ በኩል እንዲሁ የመንግሥትን ገንዘብ መበተን አይቻልም፤ የሚያስፈልጉ ዶክሜንቶች መሟላት አለባቸው። ይህን ሁሉ ባለው የሰው ሃይል እንዴት መሥራት ይቻላል? የሚለውን ገምግመን ባለው ሁኔታ አስተካክለን፤ በቀጣይነት የጀመርናቸውን መጨረስ፤ ወደ አፋር ወደ ሱማሌ ፣ ወደ አዲሱ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ ወደ አማራና ኦሮሚያም ክልሎች በስፋት እንሔዳለን።

በአጠቃላይ ሥራችንን በዚህ ሁኔታ እያስኬድን ነው። ከተባባሪዎቻችን ጋር ማለትም ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከመምህራን፣ ከሲቪክ ማሕበረሰብ፣ ከእድሮች እና ከሃይማኖት ተቋማት ጋር እንሠራለን፤ እናሳትፋቸዋለን። ከዚህ በተጨማሪ ሴቶች እና ወጣቶች እንዴት ሊሳተፉ ይችላሉ? የሚለውን እናያለን። ተሳትፎ ላይ ሴቶች አሉ፤ ነገር ግን በተባባሪነት ባለድርሻ ሆነው እንዲመጡ ለማድረግ እንፈልጋለን። ይህ እንዲሆን ሥልጠና እና ሌሎችም ብዙ መሠራት ያለባቸው ሥራዎች አሉ፤ እየተሠሩ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ምክክሩን ለማካሔድ የተዘጋጀ ፕሮግራም አለ? ለምሳሌ አዲስ አበባ ላይ መቼ ይጀመራል?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** አዲስ አበባ ላይ አበረታች ሥራዎች እየተሰሩ ነው። በአዲስ አበባ ከተማ በሀገራዊ ምክክር ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ ተወካዮችን የመለየት ሥራ ተከናውኗል። እገዛ የሚያደርጉ ተባባሪ አካላትን

**ሁሉም ነገር በንግግር ይፈታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ወሰንም ሆነ የማንነት ጥያቄ እንዲሁም ራስን በራስ ማስተዳደር እና የፍትህ ጥያቄዎች በአጠቃላይ የፖለቲካ ጥያቄዎች እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በሙሉ በትክክለኛ ምክክር ሊፈቱ የማይችሉበት ምክንያት አይኖርም**

የመለየት ሥራም ተሰርቷል። ተባባሪ አካላት የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር፣ የኢትዮጵያ ሀገር አቀፍ የዕድሮች ማህበራት ጥምረት፣ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋሟት ጉባዔ እና የወረዳ አስተዳደሮች ናቸው።

ኮሚሽኑ በከተማዋ በሚገኙ ወረዳዎች የህብረተሰብ ክፍል ተወካዮች ልየታን በሁለት የተለያዩ ምዕራፎች የሚያከናውን መሆኑን ገልጸው፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ ለተባባሪ አካላቱ ስለሂደቱ ግልፅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ኮሚሽኑ የሶስት ቀናት ሥልጠና ሰጥቷል።

በሥልጠናው ተሳታፊ የሚሆኑት ተባባሪ አካላት በየአካባቢያቸው ተሳታፊዎችን በብቃትና በገለልተኝነት በመለየቱ ሂደት ለኮሚሽኑ እገዛ ያደርጋሉ።

ሁለተኛው ምዕራፍ ኮሚሽኑ የተሳታፊዎች ልየታን በመምራት እና በማስተባበር የሂደቱን ውጤታማነት የሚከታተልበት መሆኑን አመልክተው፤ በዚህ ምዕራፍ በከተማ አስተዳደሩ ስር ከሚገኙ 119 ወረዳዎች የተውጣጡ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍል ተወካዮችን የማስመረጥ ተግባር የሚፈጸምበት ነው ።

ተመራጮቹም በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት እና በዋና ምክክሩ የሚሳተፉ ተወካዮቻቸውን እንዲመርጡ የሚደረግ ይሆናል። ለሀገራዊ ምክክሩ አመቺነት ራሳቸውን የሚገልፁበት ዋና መተዳደሪያ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ተሳታፊ የሚያደርግ መሆኑን ጠቁመው፤ እነዚህም የሃይማኖትና የማህበረሰብ መሪዎች፣ ሴቶች፣ መምህራን፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የግል ዘርፍ ተቀጣሪ ሠራተኞች፣ የንግድ ማህበረሰብ አባላት፣ ወጣቶች፣ ዕድሮች፣ በባህል እና በሙያቸው ምክንያት የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ተፈናቃዮች በወረዳ ደረጃ የሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተለይተዋል፡፡

በሌሎችም አካባቢዎች ወቅቱን ያገናዘበ ሥራ እንሰራለን። ክረምቱ የማይበረታባቸው አካባቢዎች ለምሳሌ አፋር ላይ መሥራት እንችላለን። የአፋር ተሞክሮ እንደሚያሳየው የአፋር አንዳንድ ዞኖች በጣም ሩቅ ናቸው። ዞሮ ዞሮ ግን ወደ አፋር ወደ ሱማሌ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ እያልን እንሔዳለን።

የሠላሙ ሁኔታም መረጋጋት ይኖርበታል። ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ወረዳ እና ዞን ድረስ ስንሔድ ሰላም ያስፈልጋል። ለትጥቅ ትግሉም ሆነ ለሁሉም መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ጠመንጃ ሳይሆን፤ ወደ ትጥቅ ትግል የተገባበትን አጀንዳ አምጥቶ በሰላም ተነጋግሮ የጋራ መፍትሔ መፈለግ ነው። መፍትሔው ጠመንጃ ሳይሆን ዋነኛው አማራጭ ምክክር ብቻ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ በምክክር ሁለቱም ወገኖች አሸናፊ ሆነው የሚወጡበት ነው።

በትጥቅ ትግል የሰዎች ሕይወት ይጠፋል፤ አካል ይጎድላል፤ ንብረት ይወድማል። በዚህ ድህነት ላይ ጦርነት እንደገና መጀመር፤ ከድህነት ወደ ባሰ ድህነት ማምራት እንጂ ምንም የሚተርፍ ነገር የለም። ትርፍ አለማግኘት ብቻ ሳይሆን አሸናፊ እና ተሸናፊ ይፈጠራል። በእርግጥ እንዳስተዋልነው ዛሬ አሸናፊ የሆነው ነገ ተሸናፊ ይሆናል። ጦርነት ዞሮ ዞሮ ከውድመት በስተቀር ምንም ጥቅም የማይገኝበት ነው። ዋናውና ትልቁ አማራጭ መፍትሔውም ጠመንጃ ሳይሆን አማራጩ ምክክር ብቻ ነው ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ ላይ ምን ያህል ተሳታፊዎች ይኖራሉ? እንደሌሎቹ ክልሎች ከየወረዳው የተወሰኑትን መምረጥ ነው? ወይስ አዲስ ነገር ይኖራል?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** ከየወረዳው 450 ተሳታፊ ለማድረግ አስበን ነበር። ነገር ግን ይህንን ቁጥር እንደገና እየከለስን ነው። ምክንያቱም በጣም ብዙ የሰው ሃይል እና ብዙ ገንዘብ ይፈልጋል። ቁጥሩን እያየነው ነው። ከዚህ በኋላ ከ450 በታች ይሆናል ብዬ አስባለሁ። አዲስ አበባ ውስጥ 120 ወረዳዎች አሉ። ከ120 ወረዳዎች ውስጥ ከእያንዳንዳቸው ወረዳ በርከት ያለ የሕዝብ ቁጥር ይመጣል። በአጠቃላይ ቁጥሩ በጣም ብዙ ይሆናል። በ120 ወረዳ ቢበዛ 20 ሺህ አካባቢ እና ከዛ በላይ ሊሆን ይችላል።

አሁን ጥያቄው በዛው በወረዳ እንጨርሰው ወይስ ወደ ክፍለ ከተማ እንሂድ? የሚለውን እያየን ነው። በየወረዳው ካሉ ዘጠኝ ባለድርሻ አካላት ውስጥ ተለይተው ከየባለድርሻ አካላቱ ሁለት ሁለት ይመረጣሉ፤ ስለዚህ በአጠቃላይ ከየወረዳው ወደ አስራ ስምንት ሰዎች ቁጥሩ ከፍ ሲል ወደ ሃያ ሰዎች ይመረጣሉ። እነዛ ሃያ ሰዎች ከክልሉ ወይም በአዲስ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ‹‹መፍትሔው ጠመንጃ ሳይሆን...

ከ ገጽ 10 የዞረ



አበባ ደረጃ ደግሞ ከከተማ አስተዳደሩ ከሚመረጡ ሰዎች ጋር ሆነው አጀንዳ ይሰጣሉ።

የአዲስ አበባ አጀንዳ ከእነዚሁ ተሰብሳቢዎች ይመረጣል። እነዚሁ ተሰብሳቢዎች እንደገና ለዋናው ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚወክሏቸውን ሰዎች ይመርጣሉ። በክልልም በከተማ መስተዳድርም ተመሳሳይ ነው። ምናልባት ሊለይ የሚችለው ከኢትዮጵያ ውጪ የሚኖሩት ዳያስፖራ የሚባሉት ላይ ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረጉት ነገሮች እና ሂደቶቻቸው ተመሳሳይ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ በአጠቃላይ ሃያ ሺህ የሚሆኑት ተመርጠው ከእነርሱ ውስጥ እንደገና ለሀገራዊ ምክክሩ ይመረጣሉ።**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** 120 ወረዳዎች ቢኖሩ ከየባለድርሻ አካላት ከየወረዳው 18 ሰዎች ይመርጣሉ። ከመስተዳድሩ ተሳታፊዎች ጋር ይገናኛሉ። ከዛ ውስጥ ደግሞ በፌዴራል ደረጃ በሀገራዊ ምክክሩ ደረጃ ተመርጠው ይወጣሉ። የመንግሥት ተወካዮች፣ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤት አባላት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሠራተኛ ማህበራት ፣ የንግዱ ማሕበረሰብ፣ ሴቶች በከፍተኛ ሁኔታ ይበረታታሉ። ልሂቃን፣ አርብቶ አደር፣ አርሶ አደር፣ ማንም ወደ ኋላ የሚተው የለም። እስከ አገራዊ ምክክሩ ድረስ በዚህ መልኩ የሚቀጥል ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በአማራ ክልል እና በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች የፀጥታ ችግር መኖሩ እየተገለፀ ነው። በእነዛ አካባቢ ምክክሩን የምታካሂዱት መቼ እና በምን መልኩ ነው?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** ቀናት ለመቁረጥ አሁን ላይ ያስቸግራል። ምክንያቱም የተለያዩ የየራሳቸው ምክንያቶች ይኖራሉ። ከላይ እንደገለፅኩት የመማከሪያው መንገዱን በተመለከተ በቅርቡ ይፀድቃል። ከፀደቀ በኋላ የውሎ አበል ክፍያ በደንብ ሥርዓት አስይዘን እስካሁን ያልተከፈላቸውን ተሳታፊዎች በሙሉ ከጨረስን በኋላ በአዲስ መልክ የሂሳብ ባለሙያዎችንም እንድንቀጥር ፍቃድ ተሰጥቶናል። በሚገባ ተጠናክረን መሥራት በሚገባን ደረጃ ላይ ስንደርስ እንሄዳለን። ዞሮ ዞሮ በቀጣዮቹ ስድስት ወራት ውስጥ ተሳታፊዎችን ለይተን፤ ቀርፀን፤ አውጥተን መጨረሻ ላይ ሀገራዊ ምክክር ይጀመራል የሚል ዕቅድ ይዘናል።

**አዲስ ዘመን፡- ምክክሩ የሚካሔደው በተመሳሳይ ጊዜ ነው?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** ሀገራዊ ምክክሩ በተመሳሳይ ጊዜ የሚካሄድ ነው። ማንንም የሚያገል አይደለም። ሰላም የደፈረሰባቸው አካባቢዎችም በሂደት ከጠመንጃ ይልቅ የምክክሩን ሂደት ተገንዝበው ይመጣሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። በሰሜንም፣ በደቡብም በምዕራብም በምስራቁም ያለው ሁሉም ወደ ሰላም መጥቶ የሚሻለው መመካከር ነው። ተስፋ የማደርገው ጠመንጃ ቀርቶ በሃሳብ ልውውጥ ችግር ለመፍታት ትኩረት ይሰጣል ብዬ ነው።

ሁሉም ነገር በንግግር ይፈታል የሚል እምነት አለኝ። ወሰንም ሆነ የማንነት ጥያቄ እንዲሁም ራስን በራስ ማስተዳደር እና የፍትህ ጥያቄዎች በአጠቃላይ የፖለቲካ ጥያቄዎች እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በሙሉ በትክክለኛ ምክክር ሊፈቱ የማይችሉበት ምክንያት አይኖርም።

**አዲስ ዘመን፡- ምክክሩ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል? መቼ ይጠናቀቃል?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** እርሱ አሁን አይታወቅም። ምክንያቱም ብዙ የመወያያ ርዕሶች ይመጣሉ። ቅድሚያ እና የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ርዕሶች ይኖራሉ። ምክረሃሳቡ ለተርጓሚው እና ለፈፃሚው ክፍል እያለፈ በቀጣይነት ይሔዳሉ። አንዳንዶቹ ከእኛ የጊዜ ዘመንም ሊያልፉ እንደሚችሉ እርግጠኛ ነኝ። ቢያንስ የተወሰኑት ላይ በእኛ የሥራ ዘመን እጅግ ዋና ዋና አንኳር የሆኑ፤ ሕዝብን ለማባላት በደረሱት በተወሰነ መልኩ መፍትሔ እንዲያገኙ ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን።

አንዳንድ ርዕሶች በጣም ጊዜ ሊፈጁ ይችላሉ። ዝም ብለው በአንድ ጊዜ ተወያይተው ተማክረው እጅ አውጥተው የሚለያዩበት አይደለም። ምክክር የራሱ ሥርዓት አለው። ዝግጅቱ እና ቅድመ ዝግጅቱ ስድስት ወር የፈጀው ለዚህ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የዳያስፖራው ተሳትፎ በምን መልኩ ይካሔዳል? በበይነ መረብ ነው ወይስ በምን መልኩ ይሆናል?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** በበይነ መረብ መሳተፍን በተመለከተ ቀደም ብለን አስበን ነበር። ነገር ግን አሁን የሀገር ውስጡ ሥራ ውጥረት ውስጥ ስለከተተን እንጂ፤ በቅድሚያ ዳያስፖራው ስለእኛ ሥራ በደንብ ማወቅ አለበት። ልክ ከሌሎች ምክረ ሃሳብ እንደምንሰበስበው ሁሉ፤ ከዳያስፖራውም ምክረሃሳብ እንሰበስባለን። አሜሪካን ያሉትን ለብቻቸው፣ አውሮፓ እና አፍሪካ መካከለኛው ምስራቅ ከዛ እሲያ እና የፓስፊክ ውቅያኖስ ውስጥ ያሉትን ለይተን እንቀርባለን።

በስደት ላይ ያሉ የመጀመሪያ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ሁለተኛው ትውልድ የሚባሉ የተለያዩ አሉ። ስለዚህ ሕግ እና መመሪያው በሚፈቅድላቸው መሠረት ሁላቸውም ምክረሃሳብ እንዲሰጡ ይደረጋል። በመጨረሻም ሕግ እና መመሪያው የሚፈቅድላቸው ደግሞ እርስ በእርሳቸው ተመራርጠው ዋና ሀገራዊ ምክክሩ ላይ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲሳተፉ ይደረጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ዳያስፖራዎች ተወካዮቻቸውን የሚመርጡት እንዴት ነው?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** እርሱን አልለየንም፤ ሀገራዊ ምክክር ውይይት ላይ የሚሳተፉትን በቁጥር ለመወሰን ገና ስምምነት ላይ አልደረስንም። እያብላላነው ነው። በአጠቃላይ በሀገራዊ ምክክር ሂደት ላይ ስንት ሰዎች ቢመካከሩ ያዋጣል? የሚለው በጣም ወሳኝ ነው። ምክንያቱም አስር ሺ ቢሆን በጣም ይበዛል። 100 ቢሆኑ፤ ለ120 ሚሊዮን ሕዝብ በጣም ያንሳል። ለሕዝቡ አሳታፊ ሊሆን የሚችለው ስንት ሰው ነው? የሚለውን በምክክር ውስጥ ዝም ብሎ ንግግር ሳይሆን በመረጃ የተደገፈ የሚጠቅም ንግግር፤ ተአማኒነት ያላቸው አወያዮች ያሉበት ምክክር፤ ከዚህም ባሻገር አመቻች ትልልቅ ሰዎች የማህበረሰብ መሪዎች ያሉበት ምክክር ይሆናል።

ምክክሩ የራሱ ሥርዓት እና ሒደት አለው። ቁጥሩም ከዛ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሰፊ ጊዜን ሊፈጅ የሚችል ሲሆን፤ እንዳልኩት የሚፈጀው ጊዜ አይታወቅም። ሌላ ሀገራት ላይ የተካሔደው ለምሳሌ አስር ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ቱኒዚያ ወይም  ትልቅ ሕዝብ ያላት ኬንያ 40 ሚሊዮን ሕዝብ ያውም በተወሰነ አጀንዳ ላይ እንዴት ተመካከሩ ብሎ ማየት ይቻላል። ብዙዎቹ ከእኛ እጅግ ያነሰ ቁጥር ያላቸው ሕዝቦች ናቸው። እኛ ግን ከአፍሪካ ትልቅ ቁጥር ያለውን የሕዝብ ብዛት ይዘን የተነሳን ነን።

ፓርቲዎችን ጨምረን ሁሉም እንደየሁኔታው ከየማህበረሰቡ ንቁ ተሳታፊ መሆን ስለሚገባው በጣም ሰፍቶ ለመሰብሰብ አስቸጋሪ እንዳይሆን እንጠነቀቃለን። በጣም ያነሰ እና ለጥቂቶች ብቻ የሚተውም ሳይሆን፤ በጥንቃቄ መቀመርን ስለሚፈልግ አሁን እዛው አካባቢ ደርሰናል። ነገር ግን ዋናው ስምምነት ላይ በሚደረስበት ጊዜ ይገለፃል።

ከዛ ላይ በመነሳት የዲያስፖራው ቀመርም ይወጣል። ከአምስት እስከ አስር ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ውጪ ይኖራሉ፤ ከዛ ውስጥ አዋቂዎቹ እና ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ለንግግር የሚበቁ ምን ያህል ናቸው? የሚለው ታይቶ ፤ ከዛ ውስጥ ደግሞ ምን ያህሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው? የሚለው ይለያል። ምክንያቱም ሁሉም ኢትዮጵያውያን በትውልድ ይሁኑ እንጂ በዜግነት የሌላ ሀገር ዜጎች ናቸው።

በዜግነት የሌላ ሀገር የሆኑ ሰዎች በትውልድ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው እና እትብታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ በመሆኑ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር ታሳስባቸዋለች። ስለዚህ ምክረሃሳብ የመስጠት መብታቸውን እናከብራለን። ነገር ግን ሊሳተፉ የሚገባቸውን በተመለከተ መወሰን አለበት። ምክንያቱም እዛ ላይ በጣም ሚስጥራዊ ሀአገራዊ ጉዳዮች ይኖራሉ። የአሀገሬው ሰው ብቻ የሚሳተፍባቸው ጉዳዮች ይኖራሉ። ለምሳሌ ውይይቱ የሚካሔደው ስለሕገመንግሥት ከሆነ ዜግነታቸው ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ ሰዎች አይወያዩበትም፤ እነርሱ የራሳቸው የሚተዳደሩበት ሕገመንግሥት አላቸው። በማይተዳደሩበት ሕገመንግሥት ላይ ይህንን አድርጉ ማለት ያስቸግራል። ሃሳብ መስጠት ግን ይቻላል። በምክክሩ ግን የውሳኔ ሃሳብ ስጡ ለማለት ይቸግራል። እንዲህ ዓይነት ነገሮች ይኖራሉ። ዞሮ ዞሮ መመሪያው ተዘጋጅቷል። ይህንን ግልፅ እናደርገዋለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ በውጭ የሚኖሩ የኢትዮጵያውያን ዜግነትን የቀየሩ፤ ይሳተፋሉ ማለት ነው?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** በሁሉም ላይ የመሳተፍ መብት ያላቸው አሉ። ምክረሃሳብን በተመለከተ ግን ማንኛቸውም ወገን የመስጠት መብት አላቸው ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ በዚህ ስድስት ወር ውስጥ ዲያስፖራውም ይለያል ማለት ነው?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** አዎ! ልየታው ላይ ከአጀንዳው ጋር አብሮ ቀድሞ ይሠራል።

**አዲስ ዘመን፡- እስከ አሁን ለአጀንዳ የሚሆን ሃሳብ መሰብሰቡ ምን ደረጃ ላይ ነው?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፈለገበት ሰዓት ባለው አማራጭ አጀንዳ መላክ ይችላል። ፅሕፈት ቤት በመምጣት በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ መክተት መብቱ ነው። ወደ ፊት ደግሞ እያዘጋጀን ባለነው በይነ መረብ ውስጥ በዛም መላክ ይቻላል። ይህ አንዱ ሲሆን፤ ሁለተኛ አዋጁ ላይ በጥናቶች የሚለዩ አጀንዳዎች ይኖራሉ ይላል። ለዚህ እኛም ባለሙያዎች አሉን። በጥናት የሚለዩም ካሉ እርሱንም እናያለን። ነገር ግን በአጠቃላይ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እና ማንኛውም ወገን፤ ለሀገሩ መልካም የሚያስብ፤ የሀገሩ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚያስጨንቀው ሁሉ፤ ‹‹ ወደ ፊት በጋራ እንድንሔድ የሚፈልግ ሁሉ፤ ተከባብረን እንዳንኖር የሚያደርጉ እንቅፋቶች ናቸው›› የሚላቸውን ጉዳዮች ለይተው መላክ፣ ፅፎ ማስገባት ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ከትግራይ ክልል ጋር በተያያዘ በአካል ተገኝታችሁ ተወያይታችሁ ነበር፤ ይህ ምን ላይ ደረሰ?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** በእርግጥ እኔ በወቅቱ አልነበርኩም። ከየሕብረተሰብ ክፍሉ ከተውጣጡ ሰዎች ጋር የምክክር ኮሚሽኑ አባላት ተዋውቀዋል። ነገር ግን የሔዱበት ሁኔታ ስለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ለብቻው በሀገራዊ ሁኔታ የተወያዩበት ወይም የተፈጠረላቸው መድረክ አልነበረም። ከዛ ወዲህ ግን በጎ ፍላጎት እንዲኖር፤ ሌላ ቦታ የሠራነውን መሥራት እንድንችል ጥያቄ ጠይቀናል። ደብዳቤ ፅፈንላቸዋል። መልሳቸውን እየተጠባበቅን ነው። መምጣት ትችላላችሁ በሚባልበት ጊዜ ሁሉ፤ ሕዝቡን ለማግኘት እንሠራለን። በዛ ሒደት ደግሞ ሌላ አካባቢ እንዳደረግነው ሁሉ የጋራ ሥራ እንጀምራለን።

**አዲስ ዘመን፡- ከምክክሩ ጋር በተያያዘ ከማን ምን ይጠበቃል? ሕዝቡ ምን ያድርግ?**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** ከሕዝቡ የሚጠበቀው ለሰላም ተግቶ መሥራት እና መፀለይ ነው። ሁሉም መሣሪያ ያነሱ ወገኖች መሣሪያቸውን አስቀምጠው ወደ ሰላም መምጣት አለባቸው። በቀጥታ ወደ ውይይቱ እንዲመጡ ለታጣቂዎች ጥሪ አቀርባለሁ። ለመንግሥትም መልክት ማስተላለፍ የሚፈልግ ሲሆን፤ መንግሥት ለሁሉም እጁን ዘርግቶ ምሕረት እንዲያደርግ እና ከሁሉም ጋር እንዲደራደር እጠይቃለሁ።

ደም መፍሰስ ምን እንዳመጣ እናውቃለን። በኪሳራ ላይ ኪሳራ ጨምሮልን ሄዷል። ገና ከኀዘናችን አልወጣንም። በዚህ ላይ የኑሮ ውድነቱ እና ሌሎች ነገሮችም ተጨምረው በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ በመሆኑ ለሁላችንም የምለው ሰላሙ ላይ ትኩረት እንስጥ።

በተለይ ዋና ዋናዎቹ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት እና ማህበራዊ ሚዲያውም ከምን ጊዜውም በላይ ያለፉት ሶስት ዓመታት ተመልሰው እንዳይደገሙ በሰላሙ ዙሪያ ጠንክረው እንዲሠሩ እጠይቃለሁ።

በሌላ በኩል በትግራይ በኩል መንግሽት ያደረገው ድርድር ጥይት እንዳይጮህ አድርጓል። አሁንም እልህ መጋባት እንዲቀር እጠይቃለሁ። በመሃል ኢትዮጵያ፣ በሰሜን ኢትዮጵያም ላሉ ወገኖች የሰላም ጥሪ ቢቀርብ የተሻለ ነው እላለሁ። ሁላቸውም ቁጭ ብለው ቢነጋገሩ እና ከንግግሩ ቀጥሎ ግን ሁሉም ወደ ውይይት እና ወደ ምክክር እንዲመጡ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

የሀገር ሽማግሌዎች፣ በተለይም የሃይማኖት አባቶች፣ ከአሁን በፊት እንዳደረጉት እናቶችም በተቻላቸው መጠን ልጆቻችንን መሣሪያ እንዲያስቀምጡ፤ መንግሥትም ቀርቦ እንዲነጋገሩ ግፊት እንዲያደርጉ እጠይቃለሁ። በመጨረሻም የሀገር ሽማግሌዎች በሽምግልና፣ የሃይማኖት አባቶችም በፀሎታቸው እንዲያግዙን እጠይቃለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ።**

**ፕ/ሮ መስፍን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ብቁ ሠልጣኞችን በማፍራት የፋሽን ኢንዱስትሪውን ወደፊት የማራመድ ግብ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በሀገራችን በፋሽን ዘርፍ ላይ ትምህርትና ሥልጠና ከሚሰጡ ተቋማት መካከል የምስራቅ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ አንዱ ነው። ኮሌጁ ተማሪዎችን በበርካታ ዘርፎች እያሠለጠነ ይገኛል። ከእነዚህ ዘርፎች መካከል በጋርመንት ትምህርት ክፍል የሚሰጠው የፋሽን ዘርፍ አንዱ ነው። የትምህርት ክፍሉ በፋሽን ኢንዱስትሪው ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ አዳዲስ ሃሳቦችን በማከል የተለያዩ የፋሽን ሥራዎችን ይሠራል።

ትምህርት ክፍሉ ባሉት የጋርመንት፣ የቴክስታይልና የሌዘር ዘርፎች በፋሽን ኢንዱስትሪው ላይ አንድ ርምጃ ወደፊት ሊያስኬዱ የሚችሉ ሥራዎችን ይሠራል። ከሚሰጠው ትምህርት ባሻገርም ለፋሽን ትርኢቶች ውድድሮች የሚሆኑ አልባሳትን ያዘጋጃል። በየዓመቱ በሚካሄደው ‹የቴክኒክ ሳምንት› በፋሽን ትርኢት ላይ ያዘጋጃቸውን አልባሳት ይዞ በመቅረብም ይወዳደራል። በዚህም በየዓመቱ የውድድሩ አሸናፊ በመሆን አንደኛነቱን አስጠብቆ ቀጥሏል።

ኮሌጁ በፋሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ መሆኑን የምትናገረው የኮሌጁ የጋርመንት ትምህርት ክፍል አሠልጣኝ ሀዊ ረፊሶ ፤በዘርፉ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ትገልጻለች። ሀዊ እንደምትለው፤ ኮሌጁ በፋሽን ዘርፍ በሦስቱ የትምህርት ክፍሎች የሚሰጡትን ትምህርቶች አንድ ላይ በማቀናጀት በተግባር ተርጉሞ በፋሽን ትርኢት መልኩ እንዲቀርቡ እያደረገ ነው። ኮሌጁን ለየት የሚያደርገው የሀገር ውስጥ ምርቶች መጠቀሙ እና በቀላሉ የሚገኙ ግብዓቶችን በመጠቀም በጣም ውብ ደረጃቸውን የጠበቁ አልባሳትን ማምረት መቻሉ ነው።

ለፋሽን ትርኢት የሚዘጋጁት አልበሳት ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚዘጋጁ ናቸው። እነዚህ አልባሳት በአብዛኛው የሚሠሩት በተማሪዎች ሲሆን፤ ተማሪዎቹ ክህሎታቸው የሚገልጹበትና የሚያሳደጉበት ነው። ተማሪዎቹ ዲዛይኖችን በመፍጠር፣ ያሉትን ዲዛይኖች በማስተካከል የሀገራችን ምርት በሆኑ ጨርቆች የተለያዩ አልበሳትን መሥራት እንደሚቻል የሚያሳዩበት ነው። በአሠልጣኞቻቸው ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

በኮሌጁ በፋሽን ትርኢቱ መስፈርቶች መሠረት የሀገር ውስጥ ምርቶች በመጠቀም፣ ከባህላዊ ይዘት ያላፈነገጡ አልባሳት ዲዛይን ማዘጋጀት እና ባህላዊን አልባሳትን ከዘመናዊ፣ እንዲሁም ዘመናዊን አልባሳት ከባህላዊ ጋር በመቀላቀል ዲዛይን በማድረግ ማራኪ አልባሳትን ያመርታሉ።

በፋሽን ትርኢት ላይ ለመሳተፍ ቅድሚያ በተመስጦ ሃሳብ መፍጠር ያስፈልጋል። ተማሪዎች የፈጠሩት የተመስጦ ሃሳብ አልባሳትን ዲዛይን እንዲያደርጉ ይረዳል። በተመስጦ ፈጠራው አልባሳት ቆዳ ከጨርቅ ጋር በመደባለቅ የሚሰሩ ሥራዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ በየትምህርት ክፍሉ ያሉ ተማሪዎች ተቀናጅተው በአንድ ላይ እንዲሰሩ እንደሚደረግ ትገልጻለች።

ዘርፉ የሚፈልገው የተለያዩ ፈጠራዎች አሉ የምትለው ሀዊ፤ በወዳደቁና በማያስፈልጉ ግብዓቶች፣ ለአይን የሚስቡና ማራኪ አልባሳቶች ይሰራሉ። በፋሽን ትርኢት ላይ የሚያስፈልጉ አልባሳትን ዲዛይን ለማድረግ አስራ አምስት ቀናት ይፈጃል። ሳቢ የሆኑ ሃሳቦች ተፈጥረው፣ የሚሰሩ ዲዛይኖች ተዘጋጅተው ፤ ንድፎች ተዘርግተው ወደ አልባሳት ለመቀየር ጨርቆችን ለመግዛት ያለው ሂደት ክፍተት ይፈጠራል እንጂ በትክክል ሁሉም ሂደቶች ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚሄዱ ከሆነ በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ መጨረስ ይቻላል ስትል ታብራራለች።

ሌላው ለፋሽን ትርኢቱ አስፈላጊ የሆኑ ተጓዳኝ ምርቶች (አክሰሰሪዎችን) ማለት እንደ ቦርሳ፣ ጫማዎች፣ የእጅ ጌጦች፣ የጆሮ ጌጦች፣ ጸጉር ላይ የሚደረጉ ጌጦች፣ የእጅ ጓንት ፣ የፊት ማስክ እና የመሳሳሉት ሁሉም አብረው የሚሄዱ ቁሳቁስ ስለሆኑ እንዲኖሩ ያስፈልጋል። ስለዚህ ለእነዚህን ሁሉም መያዝ የሚያስችል ሥራ አብሮ ይሰራል።

ሀዊ እንደምትለው፤ አልባሳቱ የሚዘጋጁት ለአንድና ለሁለት ለባሾች ብቻ ተብለው አይደለም። አነሰ ቢባል ሶስት ለባሾች (ሞዴሎች) የሚለብሷቸው አልባሳት ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በኮሌጁ እስከ አስር የሚደርሱ ለባሾች የሚለብሱት ልብስ ተዘጋጀቷል። አልባሳቱ በሁሉም የእድሜ ክልል ከሕጻናት ጀምሮ እስከ አዋቂዎች ድረስ ያሉ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የሚለብሷቸው ናቸው። ይህም ሁሉም ሰው መልበስ እንደሚችል ለማሳየት ይጠቅማል። ከዚህ በተጨማሪም ከተለመዱ አልባበሶች ውጭ ያሉ አልባሳትንም



ኮሌጁ በፋሽን ትርኢቱ በርካታ የአልባሳት ዲዛይኖችን አሳይቷል

እንዲሁ ማካተት አለባቸው። ቀደምሲል የተለመደው ሱሪ ከሆነ በጉርድ ቀሚስ እና በተለያዩ ነገሮች በመቀየር መልበስ እንደሚቻል ማሳየትን ይጠይቃል። እነዚህን ሁሉ ያሚሉ ለሁሉም የሚመጥኑ አልባሳት እንደሚዘጋጁ ትናገራለች።

‹‹ብዙ ጊዜ የምንሰራቸው ሥራዎች የፋሽን ኢንዱስትሪውን ሊመጥኑ የሚችሉ አልባሳት ስለሆኑ ተመራጭ ናቸው።›› ስትል ትገልጻለች። ፋሽን በባህሪው የሚደገም ኡደት ስለሆነ በተለያየ መልኩ መላልሶ በመሥራት ብቻ ሳይሆን ዘመኑ የሚፈልገው የፋሽን አይነት ምንድነው የሚለውን እንጨምርበታለን። ዘንድሮ በፋሽን ትርኢቱ ላይ ያቀረብናቸው አልባሳት በተለየ መልኩ የተመሰጥንባቸውን ሃሳቦች፤ ያልተለመዱ ግን መልዕክት ሊያስተላልፉ የሚችሉ ነገሮችን አጎልተን አሳይተናል ትላለች። ለምሳሌ ከተመሰጥንባቸውና ከተጠቅምንባቸው ሃሳቦች አንደኛው ሰፌድ ነው። በሰፌድ የአንድነትና የክብር ምልክትን ገልጸንበታል። ሌላው ደግሞ መጪው የክረምት ጊዜ መሆኑን ለመግለጽ ዝናብን የሚያሳዩ አልባሳት በጋቢ መልኩ ሰርተን በማሳየት መልዕክት ለማስተላለፍ ተጠቅመንበታል›› በማለት ገልጻለች።

በአልባሳቱ ለሀገርና ፤ ለሰው ልጆች ይጠቅማሉ ያሏቸውን መልዕክቶች ማስተላለፋቸውን ጠቅሳ፤ ትኩረታቸው የነበረው በአልባሳቱ መልዕክትን ማስተላለፍና ሀገር በቀል በሆኑ ምርቶች ባህላዊ ይዘቶችን በጠበቀ መልኩ አልባሳትን ማዘጋጀት መሆኑንና ይህንንም ማድረጋቸውን ትገልጻለች።

‹‹ለፋሽን ትርኢቱ የተጠቀምንባቸውን አልባሳትንም ሆነ ተጓዳኝ ምርቶችን (አክሰሰሪዎችን) ትርኢቱ ካለቀ በኋላ ባሉን የማሳያ ቦታዎች ላይ እንዲታዩ እናደርጋለን›› የምትለው ሀዊ፤ አብዛኛውን ጊዜ ኮሌጁን ለመጎብኘት የሚመጡ ኢንተርፕራይዞች አልባሳቱን አይተው የሚፈልጓቸው ዲዛይኖች ካሉ በማሳየት አምረተውት (አብዝተው) ለሽያጭ እንዲያቀርቡ እንደሚደረግ ትገልጻለች። ለጉብኝት የሚመጡ ተማሪዎችም እያዩ እንዲማሩበት ይደረጋል ብላለች።

‹‹ግባችን ብቁ የሆኑ ሠልጣኞችን በማፍራት የፋሽን ኢንዱስትሪውን ወደፊት እንዲራመድ ማስቻል ነው›› የምትለው ሀዊ፤ አንድ ነገር በመቅዳት አንዱን ዲዛይን ወይም ባሕል ማንጸባረቅ ላይ ብቻ ትኩረት እንደማይደረግም ትናገራለች።

ሰዎች ከሚበሉት ይልቅ ለሚለብሱት መጨነቅ ውስጥ የገቡበት ሁኔታ ይታያል የምትለው ሀዊ፣ ፋሽን ደግሞ ዛሬ ታይቶ ነገ የሚጠፋ ሳይሆን ሁሉ ጊዜ ቀጣይነት ያለው ፤ አዳዲስ ነገሮችን ለመፍጠር የሚጋብዝ፤ አእምሮን ሁሌም ለፈጠራ ዝግጁ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን ታመለክታለች። ስለዚህ በፋሽን ኢንዱስትሪው በኩል የተሻለ በመሥራት ሀገርንም ራስንም መጥቀም ይቻላል ስትል ገልጻለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ሕዝባዊ በዓላትን ለሕዝባዊ ግንኙነት

**ዋስልኝ አየለ**

ወርሐ ነሐሴ በተለይም በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች በሕዝባዊ በዓላት ይደምቃል። እነዚህ ሕዝባዊ በዓላት በተለይም የልጅ አገረዶች ቢሆኑም በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ አዋቂዎችን ይነካል። በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መድረክ ተዘጋጅቶላቸው በአደባባይ ስለሚከበሩ ከመንግሥት አመራሮች እስከ ታዋቂ ሰዎችና የሀገር ሽማግሌዎች ይገኙበታል። ምክንያቱም በዓላቱን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማክበር የግድ የአዋቂዎች ተሳትፎ ይጨመርበታልና ሕዝባዊ በዓላት ሊባሉ ይችላሉ።

እነዚህ ሕዝባዊ በዓላት በተለይም እንደ አሸንዳ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬና ሶለል የመሳሰሉ የልጅ አገረዶች ባህላዊ በዓላት በራሳቸው የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ናቸው። የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን የምናውቀው በመንግሥት አካላት አስተባባሪነት መድረኮች ተዘጋጅተው የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ ወደ ሌላ አካባቢ ማህበረሰብ በመሄድ የባህልና የተለያዩ ልምዶች ልውውጥ ሲደረግ ነው። እንደ አሸንዳ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬና ሶለል ያሉ በዓላት ግን በራሳቸው የሕዝብ ሕዝብን ግንኙነት የሚያመጡ ናቸው። አሸንዳ በትግራይ ክልል ሲከበር ከጫፍ እስከ ጫፍ ያለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይከታተለዋል። በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ መገናኛ ብዙኃን የዚያን ሰሞን የፕሮግራም ማደመቂያዎቻቸው የአሸንዳ ዘፈኖች ናቸው። የሬዲዮና ቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች የሚታጀቡት በአሸንዳ ዘፈኖችና ትዕይንቶች ነው። የማህበራዊ መገናኛ ገጾች የሚደምቁት በአሸንዳ ትዕይንቶች ነው።

በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የሚከበሩት የሻደይ፣ አሸንድዬና ሶለል በዓላት የነሐሴን ወር ደማቅ ያደርጉታል። ከተሞች እነዚህን በዓላት ለማስታወስ በሚለብሱ ሴቶችና ወጣት ወንዶች ይደምቃሉ። የአልባሳት መደብሮችና የገበያ ቦታዎች ሁሉ እነዚህን በዓላት በሚያስታውሱ ጌጣጌጦች ይደምቃሉ። በየመዝናኛ ቤቶች የሚከፈቱ ዘፈኖች እነዚህን በዓላት የሚያደምቁ ናቸው።

በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች (በተለይም አማራና ትግራይ) የሚከበሩ እነዚህ በዓላት የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቶችን ያጠናክራሉ። እነዚህ በዓላት ሲከበሩ ከሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ያሉ የባህል ቡድኖችና ታዋቂ ሰዎች ወደ አካባቢው ይሄዳሉ። ከቦታው ባይሄዱ እንኳን በመገናኛ ብዙኃንና በመድረኮች አማካኝነት ይከታተላሉ። በእነዚህ አጋጣሚዎች ሁሉ የዚያን አካባቢ ምንነቶች በሰፊው ያውቃሉ። ከዚያ አካባቢ ሰዎች ጋር በቅርበት የመተዋወቅና የመጫወት ዕድሉን ያገኛሉ።

እነዚህ ሕዝብን እርስ በእርስ የሚያስተዋውቁ በዓላት እንዳይበላሹ በጥንቃቄ ልንይዛቸው ይገባል። በተለይም ከባለፉት ዓመታት ስህተቶቻችን ልንማር ይገባል። ይህን ለማወቅ ደግሞ ግልጽ ማሳያ አለን።

ከአንድ ዓመት በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይም በትግራይ ክልል የነበረው ጦርነት የአሸንዳ በዓል ለሁለት ዓመታት ያህል እንዲቋረጥ አድርጓል። በዚህ ዓመት ደግሞ በአማራ ክልል ባለው የፀጥታ ችግር ምክንያት በሚፈለገው ልክ የሚከበር አይሆንም። ወደ አካባቢው የሚሄዱ እንግዶች አይኖሩም ማለት ነው። ይህ ማንን ይጎዳል ከተባለ ለሕጻን ልጅ ራሱ ግልጽ ነው። ግንባር ቀደም ተጎጂ የአካባቢው ማህበረሰብ ነው፤ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ጉዳቱ እንደ ሀገር ነው። የባህል ክፍተት ይፈጥራል፤ የባህል ክፍተት መፈጠር ደግሞ የትውልድ ክፍተት ይፈጥራል። ስለዚህ የእንዲህ አይነት የሕዝብ በዓላት መቋረጥ የራሱ አሉታዊ ገጽታ አለው። ይህ እንግዲህ ዋናውን የጦርነት አውዳሚነት (የሰውን ልጅ ሕይወት) ሳንጠቅስ ማለት ነው።

ወደ ሕዝባዊ በዓላቱ እንመለስ። ሕዝባዊ በዓላት ስማቸው ራሱ እንደሚያመለክተው የሕዝብ ናቸው። አክባሪያቸውም ሕዝብ ነው። እዚህ ላይ ታዲያ በትልቁ የምንታዘበው ነገር ከሕዝባዊነት አልፈው የፖለቲካ መልዕክት ማስተላለፊያ ሲሆኑ ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሕዝባዊ በዓላት ሰፊ ሽፋን ተሰጥቷቸው፣ ድጋፍ ተደርጎላቸው መከበራቸው በጣም ያስመሰግናል፤ ሕዝብን ለሕዝብ የበለጠ አስተዋውቀዋል። ዳሩ ግን በዚያው ልክ ደግሞ ከበዓላቱ ባህላዊ ይዘት ውጭ በሆነ መንገድ የምርጫ ቅስቀሳ ይመስል የፖለቲካ መልዕክት ሲተላለፍባቸውም እናያለን። የፖለቲካ መልዕክት ለማስተላለፍ የፖለቲካ መድረኮች አይበቁም ወይ?

ከሦስት ዓመታት በፊት ነው። በአንድ ሕዝባዊ በዓል ላይ አንድ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በሚቀጥለው ዓመት ለሚደረገው ምርጫ መልዕክት አስተላለፉ። በወቅቱ የምርጫ ቅስቀሳ አልተጀመረም፤ መድረኩ አካባቢ ያለ ብዙ ታዳሚ ደነገጠ። በሹክሹክታም ትዝብታቸውን ማውራት ጀመሩ። ደግነቱ ለመግባት የተፈቀደላቸው መገናኛ ብዙኃን ውስን ስለነበሩ የመጯጯህ ዕድሉን አላገኘም። ሰውየው የፖለቲካ መድረክ እስከሚያገኙ ድረስ ምን አስቸኮላቸው?

ይህ ለመንግሥት ባለሥልጣናት ብቻ አይደለም። ገለልተኛ ነን ለሚሉ ወገኖችም ጭምር ነው፤ ለሕዝቡም ጭምር ነው። ሕዝባዊ በዓላት (በተለይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው) ላይ የፖለቲካ መልዕክት ያላቸው መፈክሮችና አልባሳት አይተን እናውቃለን። የፖለቲካ ቅሬታ ያለው ሰው ፓርቲ ውስጥ ገብቶ መታገል እንጂ ስለዚያ ቡድን ዓላማ የማያውቀውን ሕዝብ ሽፋን አድርጎ የራስን ዓላማ በድብቅ ማስተላለፍ ልክ አይደለም። ባለቤት የሌለው መልዕክት ይሆናል፤ ሕዝባዊ በዓሉንም ክብር ያሳጣዋል።

በተለይ በመንግሥት ባለሥልጣናት የሚደረገው ግን የበለጠ ያስተዛዝባል፤ ምክንያቱም የተሻለ ኃላፊነት ሊሰማቸው የሚገባ እና አርዓያ መሆን ያለባቸው እነርሱ ናቸው። በሕዝባዊ በዓላት ላይ ፖለቲካዊ ንግግር ማድረግ የመንግሥትን መልዕክትም ተሰልቺ ያደርገዋል። ምክንያቱም መልዕክቱ ለዚያ በዓል ታዳሚያን ዓውዳዊ ላይሆን ይችላል። በዘመነ ኢህአዴግ የመንግሥት ባለሥልጣን ንግግር እንደ አሰልቺ ይታይ የነበረው ከይዘቱ በላይ ያለቦታው ስለሚነገር ነበር። ከእንደዚያ አይነት ልማድ አሁንም የተላቀቅን አይመስልም።

በሌላ በኩል ደግሞ የበዓላቱን ሕዝባዊነት ያደበዝዘዋል። ሊሄዱ ያሰቡ ወጣቶች ረጃጅም ፖለቲካዊ ንግግሮችን አስቀድመው በማሰብ ይሰለቻሉ ማለት ነው። ስለዚህ ሕዝባዊ በዓላት ላይ የፖለቲከኞችን መልዕክት ማስተላለፍ ባህልን ከመበረዝ አይተናነስም።

ከዚያ ውጭ ግን ሕዝባዊ በዓላት በመንግሥት ደረጃ ድጋፍ ተደርጎላቸው መከበራቸው ይበል የሚያሰኝ ነው። ምክንያቱም ለረጅም ዓመታት የነበረው ወቀሳ መንግሥት እንዲህ አይነት አገራዊ እሴቶችን አያበረታታም የሚል ነበር። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ከፍተኛ መነቃቃት ታይቷል። የባህል ቡድን ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላው አካባቢ መሄድም ተጠናክሮ ቀጥሏል። እንዲህ አይነት ባህልና ወጎቻችን ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ስፖርት


# ልዑል ገብረስላሴ በማራቶን የነሐስ ሜዳሊያ አስመዘገበ

**ቦጋለ አበበ**

በሀንጋሪ ቡዳፔስት ባለፉት አስር ቀናት ተካሂዶ ትናንት በተጠናቀቀው 19ኛው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ተጨማሪ ሜዳሊያዎችን አስመዝግበዋል።

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውጤታማ ይሆናሉ ተብለው ሲጠበቅ በነበረው የወንዶች ማራቶን የነሐስ ሜዳሊያ ተመዝግቧል። ባለፉት ሁለት ቻምፒዮናዎች በእያንዳንዱ የወርቅና የብር ሜዳሊያዎችን ማሳካት የቻሉት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች፤ ዘንድሮ ለሦስተኛ ጊዜ አሸናፊ መሆን አልቻሉም። በከፍተኛ ሙቀትና ወበቅ በታጀበው የትናንት ማለዳ የወንዶች ማራቶን ውድድር እስከ መጨረሻው እልህ አስጨራሽ ትግል ያደረገው አትሌት ልዑል ገብረስላሴ በ2:09:19 በቻምፒዮናው ለኢትዮጵያ ሦስተኛውን የነሐስ ሜዳሊያ አስመዝግቧል።

ሚልኬሳ መንገሻ በ 2:10:43 6ኛ እና ፀጋዬ ጌታቸው በ2:11:56 ሰዓት 17ኛ ደረጃን በመያዝ ያጠናቀቁ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው። አምና በኦሪገኑ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀው አትሌት ታምራት ቶላ ከብዙ ትግል በኋላ በጨጓራ ሕመም ምክንያት ከ35 ኪሎ ሜትር በኋላ ውድድሩን አቋርጦ ለመውጣት ተገዷል። በውድድሩ 85 አትሌቶች ተሳትፈው 25ቱ በነበረው



አትሌት ልኡል ገብረስላሴ በማራቶን የነሐስ ሜዳሊያ አስመዝግቧል፣

ሙቀት የተነሳ ለማቋረጥ ተገደዋል።

የዩጋንዳው ቪክቶር ኪፕላንጋት 2:08:53 በሆነ ሰዓት የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ሆኗል። ትውልደ ኢትዮጵያዊው የእስራኤል አትሌት ማሩ ተፈሪ በውድድሩ መጨረሻ ሜትሮች ልኡል ገብረስላሴ መድከሙን ተከትሎ 2:09:12 በሆነ ሰዓት የብር ሜዳሊያን ሊያጠልቅ ችሏል።

አትሌት ልዑል ገብረስላሴ በውድድሩ ወቅት የነበረው ከፍተኛ ሙቀት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች እንደ ቡድን ያሰቡትን እንዳያሳኩ ማድረጉን ገልጿል። “ውድድሩ ጥሩ ነበር ነገር ግን ሙቀቱ እየጨመረ መጥቶ ፈታኝ ሆኖብን ያሰብነውን ማሳካት አልቻልንም የነሐስ ሜዳሊያ ነው ያመጣነው ወርቅ ባለማምጣታችን ይቅርታ እንጠይቃለን” ሲልም አስተያየት ሰጥቷል።

በማራቶን ከወሰደው የነሐስ ሜዳሊያ በኋላ የኢትዮጵያ ሜዳሊያ ብዛት 9 (2 የወርቅ ፤ 4 የብርና 3 የነሐስ) ሜዳሊያዎች ደርሷል።

እስከ ወንዶች ማራቶን ማጠናቀቂያ ድረስ ከ200 በላይ ሀገራት የተውጣጡ ከ2,000 በላይ አትሌቶች ተሳትፈዋል። 42 ሀገራት የሜዳሊያ ሰንጠረዥ ውስጥ ገብተዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት 18 የዓለም ሻምፒዮናዎች በማራቶን የወሰደቻቸው ሜዳሊያዎች ብዛት 12 ናቸው። በወንዶች 3 የወርቅ፤ 6 የብርና 3 የነሐስ ሜዳሊያዎች ናቸው፡፡ ሦስቱን የወርቅ ሜዳሊያዎች ታምራት ቶላ በ2022፣ ገዛኸኝ አበራ በ2001 እንዲሁም ሌሊሳ ዴሲሳ በ2019 አግኝተዋል፡፡ 6 የብር ሜዳሊያዎችን የወሰዱት ከበደ ባልቻ በ1983፤ ሌሊሳ ዴሲሳ በ2013፤ የማነ ፀጋየ በ2015፤ ታምራት ቶላ በ2017 እንዲሁም ሞስነት ገረመው በ2019ና በ2022 እኤአ ነው፡፡ 3 የነሐስ ሜዳሊያዎችን ደግሞ ፀጋዬ ከበደ በ2009፤ ፈይሳ ሌሊሳ በ2011 እንዲሁም ታደሰ ቶላ በ2013 እኤአ ላይ አግኝተዋል።

ምሽት በተካሄደው የወንዶች 5ሺ ሜትር ፍፃሜም ኢትዮጵያውያን ልክ እንደ አምናው ሜዳሊያ ውስጥ ሳይገቡ ቀርተዋል። የ5ሺ ሜትር ክብር ባለፉት ጥቂት ዓመታት የመካከለኛ ርቀት በተለይም የ1500 ሜትር አትሌቶች ድል እየሆነ መጥቷል። ከትናንት በስቲያ በሴቶቹም ተመሳሳይ ርቀት ይህ የተስተዋለ ሲሆን፤ በትናንት ምሽት የወንዶች ውድድርም ሜዳሊያ ያስመዘግባሉ ተብለው የተጠበቁት ዮሚፍ ቀጄልቻ፣ ሀጎስ ገብረህይወትና በሪሁ አረጋዊ የታክቲክ ፍልሚያውን በድል መለወጥ ሳይችሉ 5ኛ፣6ኛና 8ኛ ሆነው አጠናቀዋል።

ኖርዌዊው ጃኮብ ኢንገብሪግሴን በርቀቱ ዳግም ቻምፒዮን ሲሆን፤ ስፔናዊው ሞሐመድ ካቲር የብር፣ ኬንያዊው ጃኮብ ክሮፕ የነሐስ ሜዳሊያ ወስደዋል።

በምሽቱ የ3ሺ ሜትር መሠናክል የሴቶች ፍጻሜም ሲምቦ አለማየሁ፣ ዘርፌ ወድማገኝ፣ ሎሚ ሙለታ ሜዳሊያ ውስጥ ሳይገቡ ቀርተዋል። ዘርፌ ወንድማገኝ 4ኛ ሆና ባጠናቀቀችበት ውድድር ትውልደ ኬንያዊቷ የባህሬን አትሌት ያቪ ዊንፍሬድ የወርቅ፣ ኬንያውያኑ ቢትሪስ ኪፕኮይችና ፌዝ ቺሮቲች የብርና የነሐስ ሜዳሊያ ወስደዋል።